ርዕስ፡- የመስኖ እና ቆላማ አካባቢ ዘርፍ የመስኖ ፕሮጀክቶች ውል አስተዳደር ግልጽነት እና ተጠያቂነት ጥናት ሪፖርት፣

**የአጥኚ ቡድን አባላት**

ዶ/ር አሰፋ መኮንን

ወ/ሮ አመለወርቅ ደጋጋ

ሰኔ 2017

አዲስ አበባ

## Contents


የጥናቱ ማጠቃለያ ( ....................................................................................................................... iv

**ምዕራፍ አንድ** ........................................................................................................................... 1

1. መግቢያ ......................................................................................................................................... 1

1.1 የጥናቱ ዳራ ................................................................................................................................ 1

1.1.1 የጥናቱ መነሻ ችግር (Statement of the Problem) ................................................................... 2

1.2. የጥናቱ ዋና ዓላማ....................................................................................................................... 3

1.2.1 የጥናቱ ዝርዝር ዓላማዎች ............................................................................................................ 3

1.3. ጥናቱ የሚሸፍናቸው ጉዳዮች፣ ...................................................................................................... 3

1.4. የጥናቱ ወሰን (Scope of the study)፣ ......................................................................................... 3

**ምዕራፍ ሁለት** ........................................................................................................................... 4

2. የጥናቱ ስልት ................................................................................................................................ 4

2.1 የጥናቱ አይነት............................................................................................................................. 4

2.2. የጥናቱ ተሳታፊዎችና ቦታዎች፣ ................................................................................................... 4

2.3. የመረጃ ምንጮችና እና የመሰብሰቢያ ዘዴዎች.................................................................................. 4

2.4. የመረጃ ምንጮች፡- ........................................................................................................................ 4

2.5. የመረጃ የመሰብሰቢያ ዘዴዎች...................................................................................................... 4

2.6 የጥናቱ የትንተና ዘዴ ..................................................................................................................... 4

**ምዕራፍ ሶስት** ............................................................................................................................. 5

3. የሰነድ ማረጋገጫ እና ትንተና ውጤቶች፣............................................................................................ 5

3.1.ፕሮጀክቶች በየዓመቱ የተመደበላቸው በጀት መጠን በተመለከተ፣ ............................................................ 5

3.2. የመስኖ ፕሮጀክቶች የምህንድስና ግዥ ግልጽነት፣ .............................................................................. 5

3.3. የመስኖ ፕሮጀክቶች በጨረታ ከፋፍሎ (lotting) ዘዴን ተጠቅሞ ለአማካሪዎች እና ተቋራጮች የተሰጣቸው ግዥ ግልጽነትን በተመለከተ፣................................................................................................................. 8

3.4. ለአንድ አማካሪ (ተቋራጭ) ከአንድ በላይ ፕሮጀክቶችን እንዲሰራ መስጠትን በተመለከተ.................................. 7

3.5. የግዥ ሰነድ መረጃዎች አያያዝ ግልጽነት፣.......................................................................................... 8

3.6. ፕሮጀክቶች በተቀመጠላቸው የማጠናቀቂያ ጊዜ እና በጀት መጠናቀቅን በተመለከተ፡- ...................................... 9

3.7. የግንባታ ዕቃዎች የዋጋ ማስተካከያን ግልጽነት በተመለከተ ............................................................... 13

3.8. የንጥል ጥናት ትንተና ውጤት (Case study Results) ..................................................................... 16

3.8.1.የመገጭ ግድብ ግንባታ እና የመስኖ ልማት ፕሮጀክት ተያያዥ ስራዎች ፣ ............................................... 16

3.8.1.1.የመገጭ ግድብ ግንባታ ፕሮጀክት ያለበት ደረጃ፣ ........................................................................ 16

3.8.1.2. የምህንድስና ግዥ አፈጻጸም ግልጽነት፣ ....................................................................................... 17

3.8.1.3.የመገጭ ግድብ ግንባታ ፕሮጀክት የውል ጊዜ እና የዋጋ ማስተካከዎች ግልጽነት፣............................... 17

3.8.1.4.የመገጭ ግድብ ግንባታ ፕሮጀክት ውል መቋረጥ ግልጽነት፣ ........ 18
3.8.2አርጆ ዲዴሳ ግድብና መስኖ ልማት ፕሮጀክት ያለበት ደረጃ ........ 19
3.8.2.1. የአርጆ ዲዴሳ ፕሮጀክት ያለበት ደረጃ፣ ........ 19
3.8.2.2. የምህንድስና ግዥ አፈጻጸም ግልጽነት፣ ........ 19
3.8.2.3. የአርጆ ዲዴሳ ግድብ ግንባታ እና ተያያዥ ፕሮጀክቶች የውል ስምምነቶች ግልጽነት፣ ........ 20
3.8.2.4. የአርጆ ዲዴሳ ፕሮጀክት የውል ማሻሻያዎች አፈጻጸም ግልጽነት፣ ........ 20
3.8.3. የወይቦ ግድብ እና ተያያዥ ስራዎች የመስኖ ልማት ፕሮጀክት ግልጽነት፣ ........ 23
3.8.3.1. የወይቦ ፕሮጀክት ያለበት ደረጃ፣ ........ 23
3.8.3.2. የምህንድስና ግዥ አፈጻጸም ግልጽነት፣ ........ 23
3.8.3.3. የፕሮጀክቱ የውል ጊዜ እና ዋጋ ስምምነቶች ግልጽነት፣ ........ 24
3.8.3.4. የወይቦ ፕሮጀክት ካሳ ክፍያ አፈጻጸም ግልጽነት፣ ........ 24
4.ፕሮጀክቶች በወቅቱ እንዳይጠናቀቁ የሚያደርጉ ምክንያቶች በተመለከተ፣ ........ 25
5.የካሳ ክፍያ ግልጽነትን በተመለከተ፣ ........ 26
6.ተሰብሳቢ ሂሳብ እና ተከፋይ ሂሳቦችን በሚመለት፤ ........ 28
7.በመስኖና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር የመስኖ ልማት ፕሮጀክቶች ውጤታማነት፣ ........ 28
**ምዕራፍ አራት** ........ 29
ዋና ዋና ግኝቶች ........ 29
**ምዕራፍ አምስት** ........ 31
የቀረቡ ምክረ ሐሳቦች ........ 31
የጥናቱ ሪፖርት ዝግጅት እና ምክክር መድረክ ዝግጅት፣ ........ 32
ማጠቃለያ ........ 33
ማጣቀሻ፡- ........ 33

## የጥናቱ አፅኅሮት ማጠቃለያ (Excutive Summary)

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በሚ/ር መ/ቤቱ የውል አስተዳደር ላይ የሙስና ተጋላጭነትን በማጥናት ግልጽነትና ተጠያቂነትን ማስፈን ነው::: ለጥናቱ ከንውን የመጀመሪያ እና ሁለተኛ ደረጃ የመረጃ ምንጮችን አገልግሎት ላይ ውለዋል:: የመጀመሪያ ደረጃ የመረጃ ምንጮች ጥልቅ ቃለ መጠይቅ እና ምልከታ ሲሆኑ፣ ከየተቋማቱ የተሰበሰቡ የተለያዩ ሰነዶች ሁለተኛ ደረጃ የመረጃ ምንጭነት ጥቅም ላይ ውለዋል:: ጥናቱ የዘርፉን አዋጆች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎች እና ማኑዋሎች የውስጥና የውጪ ኦዲት ሪፖርቶች፣ የግዥ እና የውል ስምምነት ሰነዶችን፣ ዓመታዊ የእቅድ ከንውን ሪፖርቶች፣ የፋይናንስና የካሳ ከክፍያ ሰነዶች ተዳሰዋል::

የዚህ ጥናት አቀራረብ በአብዛኛው ዓይነታዊ (qualitative) ሲሆን፣ ገላጭ ትንተና (descriptive analysis) አሀዛዊ መረጃዎችን በመተንተን ሥራ ላይ ውሏል። ከተለያዩ ምንጮች ማለትም ከሰነዶች እና ከጥልቅ ቃለ መጠይቅ የተሰበሰቡ ዓይነታዊ መረጃዎችን በመተንተን የይዘት ትንተና (Content analysis) ተጠቅሚል።

ጥናቱ ላይ የተዘረዘሩትን ዘዴዎች በመጠቀም ጥናቱ ባካተታቸው የህጎች እና የአሰራሮች አፈጻጸም፣ የግዥ አፈጻፀም፣ የውል አስተዳድር፣ የክፍያ አፈጻጸም፣ የፕሮጀክቶች አፈጻጸም የክትትልና ቁጥጥር ስርዓቱን ለመረዳት ሞክሯል:: ከእነዚህ መረጃዎች በመነሳት በመስኖ ልማት ፕሮጀክቶች የሚስተዋሉ የሙሰና ተጋላጭነት ችግሮችን በመለየት መፍትሄ ሊሆኑ የሚችሉ ምክረ ሃሳቦችን አቅርቧል::

በዚህ መሰረት የሚከተሉት ችግሮች ተለይተዋል:: በናሙና ከታዩት 8 የመስኖ ግድብ ግንባታ ፕሮጀክቶች ውስጥ 100% አማካሪዎች እና 87% ተቋራጮች ያለውድድር በቀጥታ ግዥ ዘዴ የተፈጸመ መሆኑ፤ የአንድ ፕሮጀክት የዲዛይን ዝግጅት እና የሱፐርቪዥን ሥራዎች ለአንድ አማካሪ ደርበው በመስጠት ሚዛናዊ ቁጥጥርን በማላላት፣ ግልጽነትን እና ተጠያቂነትን በመቀነስ ለጥቅም ግጭት የሚያጋልጥ ሆኖ መገኘቱ፣ በርካታ ፕሮጀክቶችን በተደጋጋሚ ለአንድ ተቋራጭ የሚሰጥ መሆኑ፣ የተቋራጮች ግዥ ሲፈፀም የምህንድስና ግምት ሳይሰራ በድርድር ዋጋ መስጠት፣ በአንድ ጨረታ ተጠቃሎ የተፈፀመ የፕሮጀክት ግዥን እንደገና በሎት ከፋፍሎ (spilit) በአዲስ ዋጋ ግዥ ማከናወን (የውል ዓይነት ለውጦች ማድረግ፣ ከፋፍሎ ውል መዋዋል፣ አዲስ የነጠላ ዋጋ መትከል፣ አዲስ የውል ማሻሻያ ማድረግ)፣ አዋጭነት በሌላቸው የመስኖ ልማት ፕሮጀክቶች ላይ ከፍተኛ በጀት መመደብ፣ በናሙና ከታዩት 8 ፕሮጀክቶች በተቀመጠላቸው የማጠናቀቂያ ጊዜ እና በጀት ባለማጠናቀቅ የወሰደው ተጨማሪ ጊዜ ከፍተኛው 157 ወራት (872%)፣ ዝቅተኛው 27 ወራት(193%) ሲሆን በአማካይ 98 ወራት (354.6%) መሆኑ፣ የጠየቀው ተጨማሪ ወጪ ከፍተኛው ብር 18,221,084,226.04 (743%)፣ ዝቅተኛው ብር 217,038,048.09 (21%) ሲሆን፣ በአማካይ ብር 6,168,408,663.96 ወይም 422.4% የደረሰ መሆኑ፣ የግንባታ ዕቃዎች የዋጋ ማስተካከያ በጊዜ ወይም በገንዘብ ወይም በዋጋ ማስተካከያ ፋክተሮች ገደብ አለመኖር፣ በፕሮጀክት አፈጻጸም ደረጃ ሳይሆን በየሎቱ ከፋፍሎ የዋጋ ማስታከያ የሚደረግ መሆኑ፣ የገበያ ዋጋ ጥናት በየጊዜው ስለማይጠና በዋጋ ማስተካከያው ላይ ከፍተኛ ጭማሪ የሚደረግ መሆኑ፣ የመስኖ ግድብ ግንባታ ፕሮጀክቶች የጥራት ችግር ያለባቸው መሆኑ፣ በሥራ አፈጻጽማቸው ለሚዘገዩ ፕሮጀክቶች ተጠያቂ አካል አለመኖር፣ ውሎችን ያለአግባብ ማሻሻል ወይም መቀየር፣ ፕሮጀክቶችን አለአግባብ ማቋረጥ እና ቶሎ ወደ ሥራ እንዲገቡ አለማድረግ፣ በሚ/ር መ/ቤቱ ከ15 ቢሊዮን ብር በላይ ተሰብሳቢ እና ከ2 ቢሊዮን ብር በላይ ተከፋይ ሂሳቦች የሚንከባለል መሆኑ፣ የተጠናቀቁ የመስኖ ልማት የፕሮጀክቶች ውጤታማነት ዝቅተኛ መሆን (ወደ ሥራ የገቡት እና ያለሙት መሬት በአማካይ 17.4% ብቻ መሆኑ) የተስተዋሉ ዋና ዋና ችግሮች ናቸው::

ለእነዚህ ችግሮች ጥናቱ መፍትሄ ሊሆኑ የሚችሉ ምክረ ሃሳቦችን አቅርቧል::

እነሱም፡ በግዥ አፈጻጸም ገንዘብ ሊያስገኝ የሚችለውን ጥቅም ለማስገኘት እና ፍትሐዊነትን (ከአድሎ ነፃ) የሆነ አፈጻጸም ለማስፈን የሚያስችለውን ግልጽ የግዥ ዘዴን ጥቅም ላይ ማዋል፤ የዲዛይን እና የሱፐርቪዥን ሥራ የሚሰሩ አማካሪዎች ሚዛኑን የጠበቀ የቁጥጥር ሥራ (Check and balance) ለመስራት እና ግልጽነትና ተጠያቂነትን ለማስፈን፣ የጥቅም ግጭትን ለመከላከል እንዲቻል የዲዛይንና

የሱፐርቪዥን የማማከር ሥራዎች በተለያዩ አማካሪዎች የሚሰራበት ሁኔታ ቢኖር፤ የፕሮጀክቱን የሥራ ክብደት፣ የጊዜ መጣበብ፣ የማሽነሪዎችና የሰው ሃይል እጥረትን ለመቅረፍ ተቋራጮች በተመሳሳይ ጊዜ የሚይዙትን የፕሮጀክት መጠን መወሰን እና ገደብ መስጠት፤ በመረጃ፣ በዝርዝር ጥናት እና ዲዛይን ላይ የተመሰረተ እና የተቀራረበ የጊዜ እና የፕሮጀክት ዋጋ ግምት መስጠት፤ ፕሮጀክቶችን በተቀመጠላቸው የማጠናቀቂያ ጊዜ፣ በጀት እና ጥራት ማጠናቀቅ ሚያስችል ስርዓት መዘርጋት፤ የዋጋ ማስተካከያዎች በጊዜ ወይም በገንዘብ ወይም በዋጋ ማስተካከያ ፋክተሮች ገደብ የሚደረግበት አሰራር መዘርጋት፤ የዋጋ ማስተካከያ በየሎቱ ከፋፍሎ ማስተካከል ሳይሆን በፕሮጀክት አፈጻጸም ደረጃ የሚስተካከልበትን አሰራር መዘርጋት፤ ባለሙያ በመመደብ እና በየጊዜው የገበያ ዋጋ ጥናት በማድረግ የሚመጣውን የዋጋ ማስተካከያ ከፍተኛ ወጪ የሚቀንስበትን አሰራር መዘርጋት፤ በተቀመጠው ውል መሰረት ለፕሮጀክቶች አፈጻጸም መዘግየት ምክንያት የሆኑ አካላት ተጠያቂ እንዲሆኑ ማድረግ እና ጉድለት በሚፈጥር አካል ላይ በተቀመጠው ውል መሰረት እርምጃዎችን መውሰድ፤ የመስኖ ግድብ ግንባታ ፕሮክቶች በተያዘላቸው ጊዜ እና በጀት እንዲጠናቀቁ የሚያስችል በስትራቴጂ የተደገፈ የክትትል እና የቁጥጥር ስርዓት መዘርጋት፤ የፕሮጀክቶችን ውጤታማነት ከፍ ለማድረግ የተጠናቀቁ የመስኖ ልማት ፕሮጀክቶች ወደ ሥራ የሚገቡበትን አሰራር በመዘርጋት ለሀገር ኢኮኖሚ ግንባታ የበኩላቸውን አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ ማድረግ የሚሉት በጥናቱ የተጠቆሙ ምክረ ሀሳቦች ተግባራዊ በማድረግ ለሙስና ተጋላጭ የሆኑ ክፍተቶችን በማስወገድ የመስኖ ልማት ፕሮጀክቶች ለሀገር የኢኮኖሚ እድገት የበኩላቸውን አስተዋፅኦ ሊያበረክቱ ይችላሉ፡፡

## ምዕራፍ አንድ

# 1. መግቢያ

ሙስና በሃገር ሁለንተናዊ እድገት ላይ ከፍተኛ የሆነ አሉታዊ ተፅእኖ በማስከተል ሃገር እንደሃገር በማይቀጥልበት ደረጃ የማድረስ ወይም ዘርፉን የማፍረስ ስጋት ሊያስከትል የሚችል ተለዋዋጭነት ባህሪ ያለው አደገኛ የሆነ የወንጀል አይነት ነው፡፡ በዚሁ መሠረት ኢትዮጵያን ጨምሮ በርካታ ሃገራት ይህን የተለዋዋጭነት ባህሪ እያሳየ ያለውን የወንጀል ዓይነት ሊመጥን የሚችል የመከላከያ ስልት በመንደፍ ስራ ላይ ለማዋል ጥረት በማድረግ ላይ ይገኛሉ፡፡ ለዚህ ችግር ሰለባ ከሆኑት ዘርፎች ውስጥ አንዱ የመስኖና ቆላማ አካባቢ ሚ/ር ነው፡፡ ይህ ጥናትም የተጠቀሱትን ችግሮች መሰረት በማድረግ የተዘጋጀ ነው። ጥናቱ በአምስት ክፍሎች የተከፈለ ሲሆን፣ በክፍል አንድ የጥናቱ ዳራ (background)፣ አላማዎች እና የጥናቱን ወሰን ይዟል፡፡ ክፍል ሁለት የጥናቱን ሥነ-ዘዴ መረጃ አሰባሰብ ሂደትና የትንተና ዘዴ አካቷል ፡፡ ክፍል ሶስት የጥናቱ ትንተና፣ በክፍል አራት የሙስና ተጋላጭነት ማጠቃለያ ግኝቶች እና የመፍትህ አቅጣጫዎች ተሰጥቷል፡፡

## 1.1 የጥናቱ ዳራ

ሙስና ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ፣ ህጋዊ እና ፖለቲካዊ ፅንሰ ሃሳብ ወይም በአጭሩ ሁለገብ (ባለ ብዙ ገጽታ) ፅንሰ ሃሳብ በመሆኑ የተነሳ የተለያዩ በጉዳዩ ላይ ጥናት ያደረጉ ግለሰቦች፣ አለም አቀፍ የልማት ድርጅቶች እና ሙስና ላይ የሚንቀሳቀሱ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ለቃሉ የሚሰጡት ትርጓሜ የተለያየ ነው፡፡ ከዚህ ውስጥም፣ የተባበሩት መንግስታት የልማት ድርጅት ሙስና የመንግስት ስልጣንን ወይም የተሰጠን ሹመት ለግል ጥቅም አላግባብ ማዋል፣ ጉቦ ወይም የማይገባ ጥቅም መቀበል፣ በስልጣን መነገድ፣ በዝምድና እና በወዳጅነት መስራት፣ በምዝበራ አማካኝነት መጠቀም ነው በማለት ቃሉን ተርጉመዋል። በአለማችን በፀረ-ሙስና እንቅስቃሴ እና ትግል ውስጥ ከፍተኛ ቦታ የያዘው መንግስታዊ ያልሆነው ድርጅት ትራንስፓረንሲ ኢንተርናሽናል ደግሞ ሙስና የተሰጠ ስልጣንን ለግል ጥቅም ሲባል አላግባብ መገልገል ማለት እንደሆነ በአጭሩ ያስቀምጣል። ድርጅቱ በሰጠው ትርጓሜ ውስጥ "የግል ጥቅም" ማለት ከገንዘብ አንስቶ፣ ቁሳቁስ፣ እንዲሁም ከቁሳቁስ ውጪ እንደ የፖለቲካ ወይም የስራ ጥቅም ማግኘት የመሳሰሉትን ያካተተ ነው። የሙስና አተረጓጉም ቢለያይም ቅሉ አብዛኞቹ ፀሐፍት ሥልጣንን ጠቅልሎ መያዝ፣ ከተጠያቂነት ራስን ነፃ ማድረግ እና ማታለልን/መዋሸትን የሚያካትቱ የሥነ ምግባር ጉድለቶች መሆናቸውን ይስማሙበታል፡፡

ሙስናን በብቃት እና በተፈለገው ሁኔታ ለመከላከል፤ ተቋማት ለሙስና የተጋለጡበትን አሰራሮችን መረዳትን ይጠይቃል። ውጤታማ የሙስና መከላከያ ዘዴዎችን ለመንደፍ እና ለመተግበር መሰረቱ

የሙስና ተጋላጭነትን መገምገም ሲሆን ይህም ተገቢውን ሙስና መከላከያ እርምጃዎችን ለመለየት እና ቅድሚያ የሚሰጣቸውን ለመምረጥ ያስችላል።

አንዳንድ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት በዓለም ላይ ከሚከናወኑ የኮንስትራክሽን ሥራዎች አብዛኛው የሚከናወነው ከመንግስት በሚመደብ ከፍተኛ በጀት ሲሆን ከሚመደበው ገንዘብ ውስጥ ከ15-20 በመቶ በሙስና ሊባክን እንደሚችል ይጠቆማል፡፡
ይህን ችግር ለመከላከል የፌደራል የሥነ ምግባር እና የፀረ ሙስና ኮሚሽን በተሰጠው ሥልጣንና ተግባር መሰረት ለበርካታ አመታት ህጎችን በማውጣት እና በመተግበር ተቋማት ላይ ሙስናና ብልሹ አሰራርን የመከላከል ተግባራት እያከናወነ ይገኛል፡፡ ይህም በተቋማት አሰራር ግልጽነትና ተጠያቂነት እንዲሰፍን ያደርጋል፡፡

### 1.1.1 የጥናቱ መነሻ ችግር **(Statement of the Problem)**

የመስኖ እና ቆላማ አካባቢ ሚ/ር የመስኖ ልማት ፕሮጀክቶች የምግብ ዋስትና ለማረጋገጥ፣ የውጪ ምንዛሬ ለማስገኘት፣ ለመንግስት እና ለባለሀብቶች ኢኮኖሚ እድገት አስተዋጽዖ ያለው ሚና ከፍተኛ ነው፡፡ ሚ/ር መ/ቤቱ በአሁኑ ጊዜ በ20 ፕሮጀክቶች ላይ የመስኖ ልማት ግንባታ እያከናወነ የሚገኝ ሲሆን ለፕሮጀክቱ የተመደበው አጠቃላይ የኢንቨስትመንት ገንዘብ ከ123 ቢሊዮን ብር በላይ ነው፡፡ ለ2017 በጀት ዓመት 8 ቢሊዮን ብር በላይ ተመድቧል፡፡ ይሁን እንጂ በዘርፉ የፕሮጀክቶች የግንባታ ግዥ እና የውል አስተዳደር ግልጽነትና ተጠያቂነት አለመኖር የፕሮጀክቶች አፈጻጸም ለረጅም ጊዜ በማጓተት መንግስት ለተጨማሪ ወጪ እንዲዳረግ አድርጎታል፡፡ ለአብነት፡-

**የአርጆ ዲዴሳ የግድብና የመስኖ ልማት ፕሮጀክት** ኦሮሚያ ክልል የሚገኝ ሲሆን ፕሮጀክቱ የማልማት አቅሙ 80,000 ሄክታር ሲሆን፣ በ18 ወራት እንዲጠናቀቅ ታስቦ ጥር 23/05/2003 ዓ.ም ውል የተፈፀመበት እና የፕሮጀክቱ የመጀመሪያው ውል መነሻ ዋጋ 755,461,980.84 ብር የተመደበ ነው፡፡ እስከአሁን የተመደበለት የኢንቨስትመንት ገንዘብ መጠን ብር 7,551,044,817.93 ነው፡፡ የግንባታው ጊዜ ከ13 ዓመት (872%) በላይ የተራዘመ እና ብር 6,795,582,837.09 (899.53%) አካባቢ ተጨማሪ ወጪ የጠየቀ ሲሆን አሁንም ያልተጠናቀቀ ፕሮጀክት መሆኑም መረጃዎች ያሳያሉ፡፡

***መገጭ ግዴብ ግንባታ ፕሮጀክት*** አማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በሰሜን ጎንደር ዞን የሚገኝ ሲሆን 17,000 ሄክታር የመስኖ እርሻ የማልማት አቅም አለው፡፡ የፕሮጀክቱ ውል የተፈረመው መስከረም 2001 ዓ.ም ሲሆን፣ ፕሮጀክቱ ሥራ የጀመረው መጋቢት 2005 ዓ.ም ነው፡፡ የመጀመያው የመነሻ የኢንቨስትመንት ዋጋው 2,451,953,789.00 ብር የተመደበለት እና በ36 ወራት እንዲጠናቀቅ የታሰበ ቢሆንም ከ15 ዓመት በላይ ተጨማሪ ጊዜ 325% የወሰደ እና በአሁኑ ሰዓት የኢንቨስትመንቱ ዋጋው ብር 18,221,084,226.04 (743.10%) ተጨማሪ ወጪ የጠየቀ ነው፡፡ ይጠናቀቃል ተብሎ የሚታሰበው ሰኔ 2018 ዓ.ም ነው፡፡ የሥራው አፈጻጸምም በ2016 በጀት ዓመት መጨረሻ 66% የደረሰ መሆኑን መረጃዎች ያሳያሉ፡፡

**የወይቦ ግድብና ተያያዥ ስራዎች የመስኖ ልማት ፕሮጀክት**

ፕሮጀክቱ በደቡብ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግስት ወላይታ ሶዶ ዞን ይገኛል፡፡ ፕሮጀክቱ ሲጠናቀቅ 3,371 ሄክታር የማልማት አቅም አለው፡፡ ለሁለቱም ሎቶች ማለት ሎት-1 እና 2 ፕሮጀክቶች የተያዘላቸው የማጠናቀቂያ ጊዜ በተከታታይ 24 እና 18 ወራት ነው፡፡ ሎት-1 ፕሮጀክት የተጀመረው ግንቦት/ 2014 ዓ.ም ሲሆን መነሻ ዋጋው 1,404,113,759.02 ቢሆንም በአሁኑ ሰዓት ተቋርጦ እንደገና ለጨረታ በሂደት ላይ ነው፡፡ ሎት-2 ፕሮጀክት ደግሞ የጀመረበት ጊዜ ግንቦት 2014 ዓ.ም ሲሆን የግንባታው የመነሻ ዋጋ ብር 1,031,374,587.03 ሲሆን፣ በአሁኑ ሰዓት የሎት-2 የኢንቨስትመንት መጠኑ ወደ በብር 1,248,412,635.12 የደረሰ ነው፡፡ ሎት-2 13 ወራት ተጨማሪ ጊዜ የተራዘመለት እና 21% ተጨማሪ ዋጋ የተመደበለት ሲሆን፣ የመሰረተ ልማት ግንባታውም በ2016 በጀት ዓመት መጨረሻ ላይ ሎት-2 16.11% እና ሎት-1 13.30% የደረሰ ሲሆን በአማካይ 14.7% ደርሷል፡፡ የፕሮጀክቱ የማጠናቀቂያ ጊዜ ግንቦት 4/2017 ዓ.ም መሆኑን መረጃዎች ያሣያሉ፡፡

ይህም ዓይነት የመስኖ ፕሮጀክት ግድብ ግንባታ ሥራዎች አፈጻጸም እና በውለታው መሰረት በተቀመጠለት ጊዜ እና በጀት አለማጠናቀቅ ለሙስናና ብልሹ አሰራር ተጋላጭ ሊያደርግ ይችላል፡፡ ተጋላጭ ሊያደርጉ ከሚችሉት ውስጥ፡ ዘርፉ ከፍተኛ መጠን ያለው ገንዘብ የሚያንቀሳቅስ መሆኑ፣ አብዛኛው የግንባታ ሥራዎች የሚደበቁ ወይም የማይታዩ በመሆናቸው፣ ግንባታው የተለያዩ የሙያ ስብጥር እና ብዛት ያለው ተሳተታፊ በመኖሩ ለቁጥጥር አመቺ አለመሆን፣ ዘርፉ በባሕሪው ውስብስብና ለማንኛውም ሰው በቀላሉ ለመረዳት አለመቻሉ ናቸው፡፡

ይህም በዘርፉ ጉቦ መቀበልና መስጠት (bribery)፣ በአደራ የተሰጠን ንብረትን አላግባብ መጠቀም (embezzlement)፣ የግል ጥቅምን ለማስገኘት የታሰበ የማታለል ተግባር (fraud) መፈፀም፣ የሰነድ ማጭበርበር፣ በጨረታ መመሳጠር እና አድሎዊ አሰራር የመሳሰሉ የሙስና ዓይነቶች የመከሰት እድላቸው ከፍተኛ ነው፡፡

የሚከሰቱ የሙስና ዓይነት ምክንያቶች፡ የህጎች መላላት፣ የቁጥጥር ማነስ፣ ደካማ የአስተዳደር ሥርዓት፣ ደካማ የአሰራር ስርዓት፣ የግለሰቦች የሥነ ምግባር ጉድለት፣ አግባብነት የሌላቸው የሥራ ግንኙነቶች፣ ግልጽነትና ተጠያቂነት አለመኖር፣ የመረጃ አያያዝ እና የቴክኖሎጂ አጠቃቀም ደካማነት፣ ምክንያቶች ሊሆኑ ይችላሉ።

እነዚህ ክስተቶች በመስኖ እና ቆላማ አካባቢ ሚ/ር ላይ የሚያስከትሉትን የሙስና ስጋት በሙስና ተጋላጭነት ዳሰሳ ጥናት መመርመር አስፈላጊ መሆኑ ይታመናል፡፡

በመሆኑም ይህን የሙስና ተጋላጭነት ለመቀነስ ሲባል በመስኖ እና ቆላማ አካባቢ ሚ/ር ውስጥ ለሙስና ተጋላጭ የሆኑ ጉዳዮችን ሙያዊና ስልታዊ በሆነ የዳሰሳ ጥናት በማካሄድና የዘርፉን የፕሮጀክት ውል አስተዳደር ግልጽነትና ተጠያቂነት አሰራር በመፈተሽ ለሙስና መከላከያ ምክረ ሀሳቦችን አቅርቧል፡፡

## 1.2. የጥናቱ ዋና ዓላማ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በመስኖ እና ቆላማ አካባቢ ዘርፍ የመስኖ ፕሮጀክት ውል አስተዳደር ግልጽነት ደረጃ በመገምገም የሙስና መከላከያ ምክረ ሀሳብ በማቅረብ ግልጽነትና ተጠያቂነትን ማስፈን ነው፡፡

### 1.2.1 የጥናቱ ዝርዝር ዓላማዎች

- የመስኖ ፕሮጀክት ውል አስተዳደር ግልጽነት ያለበትን ሁኔታ ማወቅ፤
- የመስኖ ፕሮጀክት ውል አስተዳደር ግልጽነት አለመኖር ከሙስና እና ከሥነ- ምግባር ጉድለት ጋር ያለውን ግንኙነት መፈተሽ፤
- በመስኖ ፕሮጀክቶች ውል አስተዳደር የክትትል እና የቁጥጥር ሥርዓት ግልጽነትና ተጠያቂነት መኖሩን ማወቅ፣
- በመስኖ ፕሮጀክቶች በውል አስተዳደር በተቀመጠላቸው ጊዜ፣ በጀት እና ጥራት መጠናቀቃቸውን መፈተሽ፣
- የመስኖ ፕሮጀክቶች ውል አስተዳደር ሥራዎች በተቀመጠላቸው ጊዜና በጀት አለመጠናቀቅ መንስዔዎችን መለየት፣

## 1.3. ጥናቱ የሚሸፍናቸው ጉዳዮች፣

- ጥናቱ ከሸፈናቸው የፕሮጀክት ጉዳዮች ውስጥ የመስኖ ልማት ጥናት እና ዲዛይን፣ የመስኖ ልማት ክትትልና ኮንትራክት አስተዳድር፣ የአካባቢ እና ማህበራዊ ጥበቃ፣ የመስኖ መሰረተ ልማት አስተዳደር ግልጽነትና ተጠያቂት ናቸው፡፡
- ተግባራቱም፡- የጥናትና ዲዛይን ዝግጅት፣ የግንባታ ግዥን ሂደት፡- የአማካሪና የኮንትራክተር ግዥ የጨረታ ማወዳደሪያ ዝግጅትና አፈጻጸም፣ የግንባታ ክትትልና ኮንትራት አስተዳደር ልዩነቶች እና የይገባኛል ጥያቄዎች (-Variation and Claims)፣ የፕሮጀክቱ ወሰን፣ የውል ማሻሻያዎችን፣ የዋጋ ማስተካከያዎችን፣ የካሳ ክፍያዎች፣ የፕሮጀክቶች የጥራት ሁኔታ፣ የፕሮጀክቶች ተጫማሪ ጊዜ እና ተጨማሪ በጀት አፈ.ቃቀድና አተገባበር እና የተቋረጡ ፕሮጀክቶች አወሳሰን ሰነዶችን ተዳሷል፡፡

## 1.4. የጥናቱ ወሰን (Scope of the study)፣

ጥናቱ በፌደራል ደረጃ በሚካሄደው መካከለኛ እና ከፍተኛ የመስኖ ፕሮጀክቶች ውስጥ ግንባታቸው የዘገዩ እና ከፍተኛ ወጪ የጠየቁ በናሙና የሚመረጡ የፌደራል መንግስት የሚገነባቸው ፕሮጀክቶች ናቸው፡፡ በሚ/ር መ/ቤቱ ስታንዳርድ መሰረት መካከለኛ ፕሮጀክቶች የሚባለው ከ500 እስከ 5000 ሄክታር እና ከፍተኛ ከ5000 ሄክታር በላይ የማልማት አቅያ ያላቸው ፕሮጀክቶች ላይ ነው፡፡

## ምዕራፍ ሁለት

# 2. የጥናቱ ስልት

## 2.1 የጥናቱ አይነት

የዳሰሳ ጥናቱ የሚጠቀመው ቅይጥ (mixed) የጥናት ዓይነት ነው፡፡ ይህ ዘዴ መጠናዊ (quantitative) እና ዓይነታዊ (qualitative) መረጃዎች በተመሳሳይ ጥናት ውስጥ የሚሰበሰቡበት እና የሚተነተኑበት የጥናት አካሄድ ነው።

ጥናቱ ከወሳኝ የንሞና ዘዴዎች መካከል አንዱ የሆነውን ዓላማ ተኮር ዘዴን (purposive sampling method) የተከተለ ሲሆን፣ መረጃውም ከሚመለከታቸው የመስኖ እና ቆላማ አካባቢ ሚ/ር ሃላፊዎች፣ ሰራተኞች እና ተጠቃሚዎች ተሰብስቧል፡፡

## 2.2. የጥናቱ ተሳታፊዎችና ቦታዎች፣

የሙስና ተጋላጭነት ጥናት ለማከናወን ስለዘርፍ አሠራር ጥብቅ ዕውቀት ካላቸው ሰዎች ተሳትፎና ግብዓት ተገኝቷል። በዚህ ጥናት የተሳተፉት በመስኖ እና ቆላማ አካባቢ ሚ/ር የሚገኙ 20 ከፍተኛ የአስተዳደር አባላት እና ሰራተኞች ከግንባታ ግዥ የሥራ ክፍል፣ ከፕሮጀክት ዝግጅት፣ ከፕሮጀክት ግንባታ ክትትልና ኮንትራት አስተዳደር፣ ከፕሮጀክት መሰረተ ልማት አስተዳድር፣ ከፋይናንስ የሥራ ክፍል፣ ከውስጥ ኦዲት እና ከዕቅድ በጀትና ክትትል የሥራ ክፍል ነው፡፡

## 2.3. የመረጃ ምንጮችና እና የመሰብሰቢያ ዘዴዎች

**የመረጃ ምንጮች፡-** ይህ ጥናት የመጀመሪያ እና ሁለተኛ ደረጃ የመረጃ ምንጮችን ተጠቅሟል፡፡ የመጀመሪያ ደረጃ የመረጃ ምንጮች ጥልቅ ቃለ-መጠይቆች እና ምልከታ ናቸው።

የዘርፉ ህጎች፣ ሰነዶችና ሪፖርቶች ለሁለተኛ ደረጃ የመረጃ ምንጭነት ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡

### የመረጃ የመሰብሰቢያ ዘዴዎች

በዚህ ጥናት ከዘርፉ በዓላማ-ተኮር ከተመረጡ እና ጠቃሚ ግብአት ሊሰጡ ይችላሉ ተብለዉ ከሚታመኑ ሠራተኞችና ኃላፊዎች ጋር ጥልቅ ቃለ መጠይቅ ተድርጓል፡፡ በዚህ ጥልቅ ቃለ መጠይቅ በዘርፉ ስለሚከሰቱ ብልሹ አሰራሮች፣ የሚፈጸምባቸው ምክንያቶች፣ እና ሊወሰዱ ስለሚገባቸው የመፍትሄ እርምጃዎች ትኩረት ተሰጥቷል፡፡ ሌላው ለጥናቱ ሠነዶች ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡ የመስክ ጉብኝት ተደርጓል፡፡

## 3.4.የጥናቱ የትንተና ዘዴ

በዚህ ጥናት ገላጭ ትንተና (descriptive analysis) መጠናዊ መረጃዎችን ለመተንተን ሥራ ላይ ውሏል። ከተለያዩ ምንጮች ከጥልቅ ቃለ መጠይቆች እና ከሰነዶች የተሰበሰቡ ዓይነታዊ መረጃዎችን ለመተንተን ይህ ጥናት በሰፊው ተቀባይነት ያለውን የይዘት ትንተና (content analysis) ተጠቅሟል።

# ምዕራፍ ሶስት

## 3. የትንተና ውጤቶች፣

## 3.1. በየዓመቱ ለፕሮጀክቶች የተመደበላቸው በጀት መጠን በተመለከተ፣

የመስኖ እና ቆላማ አካባቢ ዘርፍ የመስኖ ልማት ፕሮጀክቶች የምግብ ዋስትና ለማረጋገጥ፣ የውጪ ምንዛሬ ለማስገኘት እና ለባለሀብቶች እና ለመንግስት ኢኮኖሚ እድገት አስተዋጽዖ ያለው ሚና ከፍተኛ ነው፡፡ በአሁኑ ጊዜ ሚ/ር መ/ቤቱ በ20 ፕሮጀክቶች ላይ የመስኖ ልማት ግንባታ እያከናወነ የሚገኝ ሲሆን ለፕሮጀክቱ የተመደበው አጠቃላይ የኢንቨስትመንት ገንዘብ መጠን ከ123 ቢሊዮን ብር በላይ ነው፡፡ ለ2017 በጀት ዓመት ከ8 ቢሊዮን ብር በላይ የተመደበለት መሆኑን መረጃው ያሳያል፡፡

ከታች በሰንጠረዡ እንደሚታየው መንግስት ለፕሮጀክቶች በየዓመቱ የፀደቀው በጀት ከ11.8 ቢሊዮን ብር እስከ 15.1 ቢሊዮን ብር የሚመደብ ቢሆንም ከዚህ ውስጥ ለፕሮጀክቶች ሥራ ላይ የዋለው በጀት ከ7 እስከ 10.6 ቢሊዮን (በአማካይ 67.35%) ብቻ መሆኑን ጥናቱ ያሳያል፡፡

**ከ2014-2017 ዓ.ም የፀደቀ እና ሥራ ላይ የዋለ በጀት የሚያሳይ ሰንጠረዥ ቀጥሎ ቀርቧል፡፡**

**ሰንጠረዥ01**

| ዓ.ም | የፀደቀ በጀት በብር | የተስተካከለ በጀት በብር | ሥራ ላይ የዋለ በጀት በብር | በመቶኛ |
|---|---|---|---|---|
| **2014** | 16,570,000,000.00 | 14,570,000,000.00 | 9,560,000,000.00 | **65.60%** |
| **2015** | 15,120,000,000.00 | 15,120,000,000.00 | 10,640,000,000.00 | **70.36%** |
| **2016** | 7,800,000,000.00 | 12,500,000,000.00 | 8,880,000,000.00 | **70.98%** |
| **2017** | 8,840,000,000.00 | 11,840,000,000.00 | 7,010,000,000.00 | **59.23%** |
| **አማካይ** | | | | **67.35%** |

***ምንጭ***:- ከመስኖ እና ቆላማ አካባቢ ሚ/ር ሪፖርት

## 3.2. የመስኖ ግድብ ግንባታ ፕሮጄክቶች ግዥ ግልጽነትን በተመለከተ፣


የመስኖ እና ቆላማ አካባቢ ሚ/ር መ/ቤት የመስኖ ግድብ ልማት ለማልማት የአማካሪ እና የተቋራጭ ግዥ ከመፈፀሙ በፊት ፕሮጀክቶች ለሀገር ኢኮኖሚ እና ማህበራዊ ጉዳዮች ያላቸውን ጥቅም የሚያሳይ የቅድመ አዋጭነት፣ የአዋጭነት እና የአካባቢ ተፅዕኖ ጥናት ያካሂዳል፡፡ ከዚያም ዝርዝር ጥናትና የዲዛይን ሥራ ለመስራት የአማካሪ ግዥ ያከናውናል፡፡ ለግንባታ ሥራው ደግሞ የተቋራጭ ግዥ ይፈጽማል፡፡

ከታች በሠንጠረዡ እንደሚታየው በናሙና ከተመረጡ 8 የመስኖ ልማት ፕሮጀክቶች ግዥ አፈጻጸም እንደሚያሳየው ለአማካሪ 100% እና ለተቋራጭ 87.5% ግዥዎች የተፈፀሙት ያለውድድር በቀጥታ የግዥ ዘዴ ሲሆን፣ 12.5% የተቋራጭ ግዥ ብቻ በፍትሐዊ ውድድር የተፈፀመ መሆኑን መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ በፍትሐዊ ውድድር ግዥ የተፈፀመው በግልጽ ጨረታ የተከናወነው ሎት-2 የወይቦ መስኖ ልማት ፕሮጀክት ግንባታ ብቻ ነው፡፡ በተጨማሪም ለጥናት እና ዲዛይን ዝግጅት ግዥ ተፈፅሞ የተቀጠሩ አማካሪዎች የሱፐርቪዥንና የኮንትራክት አስተዳደር ሥራ 100% ደርበው እንዲሰሩ ተደርጓል፡፡

**የመስኖ ግድብ ግንባታ ፕሮጀክቶች የተፈፀመበትን የግዥ ዘዴ የሚያሳይ ሠንጠረዥ ቁ.02፣**

| ተ.ቁ | የፕሮጀክቱ ስም | ክልል | የግዥው ዘዴ | | | | | | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | ለአማካሪ ግዥ | | | ለኮንትራክተር ግዥ | | | |
| | | | ግልፅ | ውስን | ቀጥታ | ግልፅ | ውስን | ቀጥታ | |
| 1 | አርጆ ዲዴሳ ግድብና መስኖ ልማት ፕሮጀክት | ኦሮሚያ | | | ✓ | | | ✓ | |
| 2. | መገጭ ግድብና መስኖ ልማት ፕሮጀክት | አማራ | | | ✓ | | | ✓ | |
| 3 | ወይቦ መስኖ ልማት ፕሮጀክት ሎት-- 2 | ደቡብ ኢ/ያ | | | ✓ | ✓ | | | |
| 4 | ርብ መስኖ ልማት ፕሮጀክት | አማራ | | | ✓ | | | ✓ | |
| 5 | ቆጦ መስኖ ልማት ፕሮጀክት | ኦሮሚያ | | | ✓ | | | ✓ | |
| 6 | ካሊድ ዲጆ መስኖ ልማት ፕሮጀክት | ማዕከላዊ ኢ/ያ | | | ✓ | | | ✓ | |
| 7 | ምዕ/ጎዴ መስኖ ልማት ፕሮጀክት | ሶማሌ | | | ✓ | | | ✓ | |
| 8 | ከሰም መስኖ ልማት ፕሮጀክት | አፋር | | | ✓ | | | ✓ | |
| 9 | ጠቅላላ ድምር | | | | 8 | 1 | | 7 | |

**የተቋራጮችን እና የአማካሪዎችን የግዥ ዘዴ ዓይነት የሚያሳይ ግራፍ ቁ 01**




## 3.3. ለአንድ አማካሪ (ተቋራጭ) ከአንድ በላይ ፕሮጀክቶችን እንዲሰሩ የሚያደርግ ግዥ መፈፀምን በተመለከተ፣


በአሁኑ ጊዜ በዘርፉ ከሚገነቡ 20 የመስኖ ግድብ ግንባታ ፕሮጀክቶች ውስጥ አንድ አማካሪ ወይም ተቋራጭ የያዘው የፕሮጀክት ብዛት በንጽጽር የሚያሣይ ግራፍ ቀጥሎ ከታች ቀርቧል፡፡

ከታች ግራፉ እንደሚያሳየው ለአንድ አማካሪ ድርጅት ወይም ተቋራጭ ከ3--7 የሚሆኑ የተለያዩ የመስኖ ግድብ ግንባታ ፕሮጀክቶችን በተመሳሳይ ጊዜ ግዥ በመፈፀም እንዲሰሩ ተደርጓል፡፡ ይህም የሥራ ክብደትን፣ የጊዜ መጣበብን፣ የማሽነሪዎች እና የሰው ሃይል እጥረትን ስለሚፈጥር ግንባታው በወቅቱ (በታቀደለት ጊዜ) እንዳይጠናቀቅ አድርጎታል፡፡ የፕሮጀክቶች ግንባታ በጊዜ አለመጠናቀቅ  የግንባታ ጥራቱ እንዲጓደል ስለሚያደርግ መንግስት አላግባብ ለተጨማሪ ወጪ እና ለይገባኛል ጥያቄ እንዲጋለጥ ያደርጋል፡፡ የጥራት ጉድለት ሲፈጠር አግባብ ያልሆነ ድርድርን (Compromised) በመፍጠር ለሙስናና ብልሹ አሰራር እንዲጋለጥ ሊያደርግ ይችላል፡፡

**አማካሪዎች በግዥ የያዙት የፕሮጀክት ብዛት ከሚገነቡ 20 ፕሮጀክቶች ያለቸው ድርሻ ግራፍ ቁጥር 02፣**




**ግራፍ 03 ተቋራጭ ድርጅቶች መግዥ የያዙት የመስኖ ፕሮጀክቶች ብዛት ከዘርፍ አጠቃላይ ፕሮጀክቶች አንጻር፣**




## 3.4.የመስኖ ፕሮጀክቶችን በጨረታ ከፋፍሎ (lotting) ዘዴን ተጠቅሞ ለተቋራጮች እና አማካሪዎች የተሰጣቸው ግዥ ግልጽነትን በተመለከተ፣

የመስኖ ግድብ ግንባታ ፕሮጀክት ሥራ ጨረታ ወጥቶ ግዥ ከተፈፀመ እና ሥራ ከተጀመረ በኋላ አንድን ፕሮጀክት በሎት ከፋፍሎ ፕሮጀክቱን ለያዙት ተቋራጭ እና አማካሪ መስጠት አለ፡፡ ለአብነት፡

የኦሮሚያ ኮንስትራክሽን ኮርፖሬሽን የአርጆ ዲዴሳ ፕሮጀክት አካል የሆኑትን አርጆ ዲዴሳ ግድብ ግንባታን እና ተዛማጅ ሥራዎች ፣ ሎት-1 አርጆ ዲዴሳ የውሃ ማስተንፈሻና የቀኝ ውሃ ማስወጪያ ግንባታ፣ ሎት-2 አርጆ ዲዴሳ የግራ ውሃ ማስወጪያ ግንባታ፣ ሎት-3 አርጆ ዲዴሳ የውሃ ማስተንፈሻና የቀኝ ውሃ ማስወጪያ የፓይል መሰረት ግንባታ በማለት ከፋፍለው እንዲሰጡ የተደረገ ሲሆን፣ የኦሮሚያ ኢንጂነሪንግ ኮርፖሬሽንም በተመሳሳይ እነዚህን በሎት የተከፋፈሉ ሥራዎች የማማከር ሥራ ይዟል፡፡

የአማራ ውሃ ሥራዎች ኮርፖሬሽን ደግሞ አጅማ-ጫጫ ሎት-1 ቀኝ የውሃ ማስወጫ ግንባታ፣ አጅማ-ጫጫ ሎት-2 ግራ የውሃ ማስወጫ ግንባታ እና አጅማ-ጫጫ ሎት-3 ግድብ እና ተዛማጅ ግንባታዎች በሎት የተከፋፈሉን የፕሮጀክቱ አንድ አካል የነበሩ ነገር ግን በሎት ከፋፍሎ የተሰጡ ሲሆን፣ ለ3ቱም ሎቶች አማካሪ የልህቀት ዲዛይንና ሱፐርቪዥን ኮርፖሬሽን መሆኑን ጥናቱ ያሳያል፡፡

ፕሮጀክቶችን በሎት ከፋፍሎ የሚሰጡበት ምክንያት በውሉ ላይ አዳዲስ የነጠላ ዋጋ ለመትከል፣ አዲስ ምጣኔ እና አዲስ የዋጋ ማስተካከያ ለማድረግ፣ አዲስ የውል ስምምነቶችን ለመዋዋል ሲሆን፣ መንግስት በዚህ ሁኔታ ከፍተኛ የፕሮጀክት ተጨማሪ ወጪ እንዲያወጣ አድርጎታል፡፡

## 3.5. የግዥ ሰነድ መረጃዎች አያያዝ ግልጽነት፣

የመንግስት መ/ቤቶች የግዥ መረጃዎችን እና የውል መዝገቦችን የመጠበቅ ሀላፊነት አለባቸው፡፡ እያንዳንዱ የመንግስት መ/ቤቶች የግዥ ተግባራትን፣ የተዋዋሏቸው ውሎች እና ስምምነቶችን በሚመለከት የተሟላ ሰነድ ወይም መረጃ ያለው መሆኑን ማረጋገጥ አለበት፡፡

የተለያዩ ግዥዎችን የሚመለከቱ ጉዳዮች የያዙ ሰነዶች ለወደፊት በማጣቀሻነት እንዲያገለግሉና ለቁጥጥር ዓላማዎችም እንዲውሉ በፌደራል መንግስት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 648/2001 አንቀፅ 73 በተገለፀው መሰረት በሚወጣው ደንብ ላይ ለፋይናንስ ሰነዶች የቆይታ ጊዜ የተገለፀውን ዓመት መጠበቅ አለባቸው በሚል የተደነገገ ቢሆንም በሚ/ር መ/ቤቱ በጨረታ ሂደት ወቅት መገኘት ካለባቸው ሰነዶች ውስጥ የፍላጎት መግለጫ መጠየቂያ፣ ለቀጣይ ውድድር የተመረጡ ዕጩ ተወዳዳሪዎች፣ የጨረታ ሰነዶች፤ ከጨረታ ጋር በተያያዘ ከአቅራቢዎች ጋር የተደረጉ የደብዳቤ ልውውጦች፣ የተጫራቾች መጫረቻ ሰነዶች፣ የጨረታ አከፋፈት ሂደትን የሚገልፁ ሰነዶች፣ የጨረታ ማስከበሪያ በተመለከተ የተያዘ ሰነድ፣ ለሚመለከተው አካል ለውሳኔ የቀረቡ አግባብነት ያላቸው የግምገማ ሪፖርቶችና የውሳኔ ሀሳብ ቃለ ጉባኤዎች ሁሉም በአግባቡ አለመያዛቸውን ወይም ጭራሽ አለመኖራቸውን ለማወቅ ተችሏል፡፡ ለአብነት ከታች በሰንተረዥ እንደሚታዩት በናሙና ከተመረጡ 8 ፕሮጀክቶች ውስጥ የአማካሪ ግዥ 25 በመቶ የሚሆኑት የተሟላ መረጃ ያላቸው ሲሆን፣ 75 በመቶ የሚሆኑት ፕሮጀክቶች የግዥ ሰነዶች መረጃ የሌላቸው ወይም የተሟላ የግዥ ሰነዶችን ማግኘት አለመቻሉን ያሳያል፡፡ የተቋራጮች የግዥ ሰነድ ደግሞ 37.5 በመቶ የተሟላ መረጃ ያላቸውና 62.5 በመቶ የተሟላ የግዥ መረጃ የሌላቸው መሆኑን መረጃዎች ያሳያሉ፡፡

**የተሟላ የግዥ ሰነድ ያላቸው እና የሌላቸው የአማካሪዎችና የተቋራጮች ግዥ የሚያሳይ ሰንጠርዥ03፣**

| በናሙና የታዩ ግዥዎች | የአማካሪዎች ግዥ | በመቶኛ | የተቋራጮች ግዥ | በመቶኛ |
|---|---|---|---|---|
| በናሙና የታዩ ፕሮጀክቶች ብዛት | 8 | 100% | 8 | 100% |
| የተሟላ የግዥ መረጃ ያላቸው ፕሮጀክቶች ብዛት | 2 | 25% | 3 | 37.50% |
| የተሟላ የግዥ መረጃ የሌላቸው ፕሮጀክቶች ብዛት | 6 | 75% | 5 | 62.50% |

## 3.6. ፕሮጀክቶች በተቀመጠላቸው የማጠናቀቂያ ጊዜ እና በጀት መጠናቀቅን በተመለከተ፡-

የመስኖ ግድብ ግንባታ ፕሮጀክት ስኬት በተለያዩ ምክንያቶች (Factors) ሊለካ ይችላል፡፡ በአብዛኛው የፕሮጀክቶች አፈጻጸም በ3 መለኪያዎች ሊለካ ይችላል፡፡ እነሱም የጊዜ፣ የበጀት እና የጥራት መለኪያዎች ናቸው፡፡ የፕሮጀክቶች የአፈጻጸም የጊዜ መጓተት በወጪ እና በጥራት ላይ ቀጥተኛ ተፅዕኖ አለው (ማክዶላልድ ዲ.ኤች 1983)፡፡

ጊዜ የፕሮጀክት ስኬት መለኪያ ቢሆንም፣ በአገራችን ያሉ አብዛኞቹ  የመስኖ ግድብ ግንባታ ፕሮጀክቶች ማለት ይቻላል በተቀመጠላቸው የማጠናቀቂያ ጊዜ እንደማይጠናቀቁ የፕሮጀክቶች አፈጻጸም መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ የፕሮጀክቶች አፈጻጸም ተጨማሪ ጊዜ የተለያዩ ሙሑራን የተለያዩ ትርጉም ቢሰጡትም የጋራ የሚያደርገው ግን በውሉ መሰረት ሁለቱ ወገኖች ከተስማሙበት እና ከታቀደው የፕሮጀክት ማጠናቀቂያ ጊዜ ማለፍ ተጨማሪ ጊዜ ይባላል፡፡ አንድ ፕሮጀክት በወቅቱ አለመጠናቀቅ ብዙ ተፅዕኖዎች አሉት፡፡ ከእነዚህ ውስጥ የማጠናቀቂያ ጊዜን ማራዘም፣ ተጨማሪ በጀት መጠየቅን እና የይገባኛል ጥያቄዎችን ማስነሳት ይጠቀሳሉ፡፡ የሥራ ትዕዛዞች ለውጥ (Variation Change) በፕሮጀክት አፈፃፀም ደረጃ ሳይሆን በየሎቶች ከፋፍሎ በመተግበር የግንባታ ትዕዛዝ ለውጥን ከ25 በመቶ በላይ እንዲሆን እና አዳዲስ የውል ማሻሻያዎችን ማድረግ፣ እንዲሁም የስራ ለውጥ የሚደረግበትን ወሰን (Scope) አለመወሰን ለፕሮጀክቶች ተጨማሪ ጊዜ በማራዘም መንግስት ለተጨማሪ ወጪ እንዲጋለጥ አድጎታል፡፡

**ሠንጠረዥ ቁጥር 04 በናሙና የተመረጡ የመስኖ ግድብ ግንባታ ፕሮጀክቶች ተጨማሪ ጊዜ የሚያሳይ፣**


**ምንጭ፡**- ከመስኖ እና አካባቢ ሚ/ር እና ከኦጥኘው ቡድን ስሌት፣

ከላይ በሰንጠረዡ ከሚታዩ ፕሮጀክቶች ውስጥ ከፍተኛውን ተጨማሪ ጊዜ የጠየቀው አርጆ ዲዴሳ ግድብ 157 ወራት ወይም 13 ዓመት (872%)

| **ተ.ቁ** | **የፕሮጀክት ስም** | **ፕሮጀክቱ ውሉ የጀመረበት ጊዜ** | **ፕሮጀክቱ የሚጠናቀቅበት ጊዜ** | **ለፕሮጀክቱ የተሰጠ ማጠናቀቂያ ጊዜ በወራት** | **የተሻሻለው የፕሮጀክቱ ማጠናቀቂያ ጊዜ በወራት** | **የፐረቶጀክቱ ማጠናቀቂያ ተጨማሪ ጊዜ በወራት** | **የተጨማሪ የማጠናቀቂያ ጊዜ በመቶኛ** | **ፕሮጀክቱ የደረሰበት ደረጃ** |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1. | አርጆ ዲዴሳ ግድብ ግንባታና መስኖ ልማት ፕሮጀክት | የካቲት 2003 ዓ.ም | ግንቦት 23/2017 ዓ.ም | 18 | 175 | **157** | 872% | 60.78% በአማካይ |
| 2. | የመገጭ ግድብ ግንባታ ፕሮጀክት | መጋቢት 2001 ዓ.ም | ሰኔ /2018 ዓ.ም | 48 | 204 | **156** | 325% | 66% |
| 3 | የታችኛው ርብ መስኖ እና ድሬኔጅ ፕሮጀክት | መስከረም 21/2000 ዓ.ም | ጥር08/ 2014 ዓ.ም | 48 | 164 | **120** | 250% | 97.97% |
| 4 | የወይቦ መስኖ ልማት ፕሮጀክት ሎት--2 | ጥቅምት 2014 ዓ.ም. | ግንቦት 04 /2017 ዓ.ም | 14 | 41 | **27** | 192.9% | 14% |
| 5. | የካሌድ ጂጆ መስኖ ልማት ፕሮጀክት | ጥቅምት 2013 ዓ.ም. | ሰኔ/ 2018 ዓ.ም. | 24 | 56 | **32** | 133.3% | 24.81% |
| | አማካይ | | | | | **98** | **354.6%** | |
| | | | | | | | | |

ሲሆን፣ ዝቅተኛው የካሊ ዲጆ ፕሮጀክት 32 ወራት (133.3%) ነው፡፡ እነዚህ በናሙና የተመረጡ 5 ፕሮጀክቶች በአማካይ 98 ወራት ወይም 8 ዓመት (355%) ተጨማሪ ጊዜ የጠየቁ መሆኑን መረጃው ያሳያል፡፡ የፕሮጀክቶች አፈጻጸም ተጨማሪ ጊዜ መጠየቅ ለተጨማሪ ወጪ እና ለይገባኛል ጥያቄ ማስነሳት ምክንያት በመሆኑ መንግስትን ለከፍተኛ ተጨማሪ ወጪ እየተዳረገ የሚገኝ መሆኑን ያሳያል፡፡

**የፕሮጀክቶች ተጨማሪ ማጠናቀቂያ ጊዜ በመቶኛ ግራፍ 04**




### 3.7. በናሙና የከተመረጡ የመስኖ ግድብ ግንባታ ፕሮጀክቶች ተጨማሪ ወጪን የሚያሳይ ሠንጠረዥ 05፣


**ምንጭ፡-** ከመስኖ እና ቆላማ አካባቢ ሚ/ር እና ከአጥኚው ቡድን ስሌት.

ከላይ በሰንጠረዥ እንደሚታው ከፍተኛው ተጨማሪ ወጪ የጠየቀው የመገጭ ግድብ ፕሮጀክት ሲሆን **ከ18 ቢሊዮን** ብር በላይ ወይም **743%**

| ተ.ቁ | የፕሮጀክት ስም | የፕሮጀክቱ የውል የመነሻ ዋጋ መጠን በብር | አሁን ላይ የተመደበው በጀት መጠን በብር | የፕሮጀክቱ ተጨማሪ ወጪ መጠን በብር | የተጨማሪ ወጪ በመቶኛ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1. | አርጆ ዲዴሳ ግድብ ግንባታና መስኖ ልማት ፕሮጀክት | 755,461,980.84 | 7,551,044,817.93 | 6,795,582,837.09 | 899.53% |
| 2. | የመገጭ ግድብ ግንባታ ፕሮጀክት | 2,451,953,789.37 | 20,673,038,015.41 | 18,221,084,226.04 | 743.10% |
| 3 | የታችኛው ርብ የፍሳሽ ማስወገጃ ፕሮጀክት | 1,336,274,358.08 | 3,639,891,362.43 | 2,303,617,004.35 | 172% |
| 4 | የወይቦ መስኖ ልማት ፕሮጀክት | 1,031,374,587.03 | 1,248,412,635.12 | 217,038,048.09 | 21 % |
| 5. | የካሌድ ጂጆ መስኖ ልማት ፕሮጀክት | 1,195,278,795.76 | 4,500,000,000.00 | 3,304,721,204.24 | 276.5% |
| | **ድምር** | | | **30,842,043,319.81** | |
| | **አማካይ** | | | **6,168,408,663.96** | **422.4%** |

መንግስት ተጨማሪ ወጪ የጠየቀ ሲሆን፣ በመቶኛ ሲታይ ደግሞ ከፍተኛ ሆኖ የሚገኘው አርጆ ዲዴሳ ፕሮጀክት **899.5%** ነው፡፡ አሁን ባለው ሁኔታ ዝቅተኛ ወጪ የሚታየው የወይቦ ፕሮጀክት ሲሆን የጠየቀው ተጨማሪ ወጪ **217** ሚሊዮን ብር በላይ ወይም **21%** አካባቢ ቢሆንም የአፈጻጸም ደረጃው ግን **14%** ላይ ነው**፡፡** ከላይ በሰንጠረዡ የሚታዩት 5ቱ ፕሮጀክቶች መንግስትን የጠየቁት ተጨማሪ ወጪዎች **በአማካይ ከ6 ቢሊዮን** ብር በላይ ወይም **422.4%** መሆኑን ጥናቱ ያመላክታል፡፡ መንግስት በአርጆ ዲዴሳ ግድብ ፕሮጀክት እና በመገጭ ግድብ ግንባታ ብቻ ከ25 ቢሊዮን ብር በላይ ተጨማሪ ወጪ የጠየቀው ሲሆን በ5 ፕሮጀክቶች ጠቅላላ ድምር ከብር 30.8 ቢሊዮን በላይ መንግስትን ተጨማሪ ወጪ ያስወጣ መሆኑን መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ እስካሁን እነዚህ 5 ፕሮጀክቶች ያልተጠናቀቁ ናቸው፡፡

**ግራፍ 05 የመስኖ ፕሮጀክቶች ያስከተሉት ተጨማሪ ወጪ መጠን በብር.**




**የመስኖ ግድብ ግንባታ ፕሮጀክቶች መዘግየት ዋና ዋና ምክንያቶች፡-**

የየአዋጭነት ጥናትና ዲዛይን ሳይጠናቀቅ ፕሮጀክቶችን መጀመር፤ የመስኖ ጥናትና ዲዛይን ፕሮጀክቶች በበቂ ቅድመ ዝግጅት ላይ ተመስርቶ አለመጀመራቸው፣ ዝርዝር ጥናቱ አለማድረግ፣ ዲዛይኑ ከመዘጋጀቱ በፊት የግንባታ ሥራው እንዲጀመር ማድረግ፣ አማካሪ ሳይኖር የፕሮጀክት ግንባታ ስራ መጀመር፤ የፕሮጀክት ወሰን ግልፅ ሳይሆን የፕሮጀክት ግንባታ መጀመር፣ ባልተጠናቀቀ ዲዛይን ግንባታ ማካሄድ፣ የተሳሳተ ቅድመ ሳይት ምርመራ ማድረግ፣ ለአንድ ተቋራጭ በተመሳሳይ ጊዜ ብዙ ፕሮጀክቶችን እንዲሰራ መስጠት፣ በተደጋጋሚ የዲዛይን ለውጥ ማድረግ፣ የፕሮጀክቱን ወሰን ደጋግሞ መቀየር፣ የካሳ ክፍያ በወቅቱ አለማጠናቀቅ፣ የሥራ ትዕዛዝ መቀየር፣ ክፍያ ማዘግየት፣ አማካሪዎች እና ተቋራጮች ፕሮጀክቱን የማስተዳደር ልምድ ማነስ እና የክትትልና ቁጥጥር አቅም ማነስ የፕሮጀክት ግንባታዎች እንዲዘገዩ የሚያደርጉ ምክንያቶች ናቸው፡፡

## 3.8. የግንባታ ዕቃዎች የዋጋ ማስተካከያን ግልጽነት በተመለከተ፡-

በፌደራል መንግስት የግዥ መመሪያ ሰኔ 2002 ዓ.ም ምዕራፍ 16 አንቀጽ 14 ንዑስ አንቀፅ 2 እንደተገለጸው የመንግስት መ/ቤቱ ለግንባታ ሥራዎች ውሉ ተፈጻሚ መሆን ከጀመረበት 12 ወራት በኋላ ለሚኖር ግዥ የዋጋ ለውጥ ወይም ማስተካከያ ማድረግ እንደሚቻል በጨረታ ሰነዱ ላይ ማመላከት እንዳለበት ተደንግጓል፡፡ በውል ስምምነቱ መሰረት የግንባታ ሥራውን ለማጠናቀቅ ከ12 ወራት በላይ የሚፈጅ መሆኑ የተረጋገጠ ሲሆን፣ የዋጋ ማስተካከያ እንዲደረግበት በሚመረጠው ስብስብ ላይ ኤጀንሲው ወይም ስታትስቲክስ ኤጀንሲ ጠቋሚ ዋጋ መረጃ (የዋጋ ኢንዴክስ) መስጠት መቻሉ ሲረጋገጥ ነው በሚል ተደንግጓል፡፡ የመንግስት ግዥ መመሪያ ምዕራፍ 16

ብሔራዊ ግልጽ ጨረታ አፈጻጸም አንቀጽ 14 ንዑስ አንቀጽ 3 እንደሚገልፀው ለግንባታ ሥራ የሚደረግ ግዥ **የዋጋ ማስተካከያን** በተመለከተ ማንኛውም ከግንባታ ሥራ ግዥ ጋር በተያያዘ የሚደረግ የዋጋ ማስተካከያ አሰራሮችን ተከትሎ በመደበኛ የጨረታ ሰነድ ላይ የተመለከተውን ቀመር በመጠቀም መሰላት አለበት ይላል፡፡ እነሱም 16/14(9) የዋጋ ማስተካከያ ተግባራዊ የማድረግ ሂደት ውስጥ በማስተካከያው ምክንያት የተፈጠረው ልዩነት ከግንባታ ሥራው ጠቅላላ የውል ዋጋ ከ25 በመቶ በሚበልጥበት ጊዜ የዋጋ ለውጡን ተቀብሎ ግዥውን መቀጠሉ ኢኮኖሚያዊ ጥቅም የሚያስገኝ መሆኑ ተረድቶ ተገቢውን ውሳኔ መወሰን እንዲችል የመ/ቤቱ የበላይ ኃላፊ እንዲያውቀው መደረግ ይኖርበታል በሚል ተደንግጓል፡፡

ይሁን እንጂ በተቋራጮችም ሆነ በአማካሪዎች ግዥ ሰነድ ውስጥ የተቀመጠ የዋጋ ማስተካከያም ሆነ የቀመር ስምምነት የሚያሳይ ማስረጃ በሌለበት፣ እንዲሁም በግንባታ ውል ልዩ የኮንትራት ስምምነቱ ላይ GCC 62.7 እና 62.13 የዋጋ ማስተካከያ እንደማይደረግ በስምምነቱ በግልጽ ተቀምጦ እያለ፣ የፕሮጀክቱ ባለቤት ለተቋራጮች እና አማካሪዎች የዋጋ ማስተካካያ እንዲደረግላቸው የመንግስት ግዥ እና ንብረት አስተዳድር ባለስልጣን በደብዳቤ በመጠየቅና በማስፈቀድ የዋጋ ማስተካከያው ተግባራዊ እያደረገ ይገኛል፡፡ እየተደረገ ያለው የዋጋ ማስተካከያ በመንግስት የግዥ ህግ መሰረት በጨረታ ውድድር ጊዜ አስቀድሞ ባልተቀመጠ ቀመር፣ የውል ስምምነት እና በግንባታ ውል ላይ የዋጋ ማስተካከያ ተግባራት አይደረግም ተብሎ በግልጽ በተቀመጠበት ሁኔታ እና ተቋራጩም በዚህ ውል ተስማምቶ ከፈረመ እና ሥራውን እያከናወነ ባለበት ሁኔታ ከመንግስት የግዥ ህግ ውጭ የዋጋ ማስተካከያ በማድረግ የፕሮጀክቶችን ግንባታ አሰራር ግልጽነት የጎደለው እንዲሆን በማድረግ መንግስት ተጨማሪ ወጪ እንዲያወጣ አድርጎታል፡፡

ሌላው የዋጋ ማስተካከያ ከሚደረግባቸው የግንባታ ዕቃዎች ውስጥ ሲሚንቶ፣ ብረት፣ ነዳጅ፣ የሰው ሃይል ወዘተ… ይገኝበታል፡፡ እነዚህ የግንባታ እቃዎች ወጥ የሆነ የዋጋ ማስተካከያ ማባዣ(factors) የላቸውም፡፡ ክብደቱ (Weightage) 60 በመቶ የግንባታ ዕቃዎች ዋጋ የሚስተካከልባቸው ሲሆኑ፣

40 በመቶ ግን ማስተካከያ የማይደግባቸው ዕቃዎች ተብሎ የተቀመጡ ቢሆንም፣ ክብደቱ በምን መስፈርት እና እንዴት እንደተመረጡ የሚታወቅ ነገር የለውም፡፡

**የዋጋ ማስተካከያ የተደረገላቸው ፕሮጀክቶችን የሚያሳይ ሠንጠረዥ 05፣**

ከላይ በሰንጠረዡ እንደሚታየው ከፍተኛ የዋጋ ማስተካከያ የተደረገበት ቄጦ የአናት ሥራ ፕሮጀክት ሲሆን፣ ለ400 ሄክታር የመስኖ ልማት ግንባታ እና በ**49.5%** የሥራ አፈጻጸም አንጻር ከመነሻው የፕሮጀክት ዋጋ ጋር ሲነጻጸር ብር 603,120,831.20 ወይም **65.9%** የዋጋ ማስተካከያ የተደረገለት መሆኑን ጥናቱ ያሳያል፡፡ የወይቦ መስኖ ግንባታ ሎት-2 በ8.20% የሥራ አፈጻጸም ከፕሮጀክቱ የመነሻ ዋጋ

| ተ.ቁ | **የፕሮጀክቱ ሥም** | **ተቋራጭ** | **የሚለማው መሬት በሄክታር** | **የውል መነሻ ዋጋው መጠን በብር** | **የዋጋ ማስተካካያ መጠን በብር** | **በመቶኛ** | **ሥራው ያለበት ደረጃ** |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ጨል-ጨል ሎት-2 | ኦሮሚያ ኮንስትራክሽን ኮርፖሬሽን | 4,145 | 821,632,409.47 | 457,441,341.95 | 56% | 98.10% |
| 2 | አርጆ ዲዴሳ ግድብ ገንባታ | ኦሮሚያ ኮንስትራክሽን ኮርፖሬሽን | 80,000 | 755,461,980.84 | 333,198,071.46 | 44% | 95.95% |
| 3 | አርጆ የውሃ ማስተፈሻ | | | 2,646,000,522.44 | 169,945,662.33 | 6.4% | 29.21% |
| 4 | ቄጦ ፕሮጀክት | ሀቨሪም ኮንስትራክሽን | 400 | 915,701,573.72 | 603,120,831.20 | 65.9% | 49.5% |
| 5 | ከሰም ድብና መስኖ ሪሀብ. ፕሮጀክት | ኢ.ኮን.ሥራዎች ኮርፖሬሽን | 1720 | 632,110,514.07 | 294,170,441.05 | 47% | 51.57% |
| 6 | አጅማ ጫጫ ፕሮጀክት ሎት1 | አማራ.ውሃ ሥራዎች ኮርፖሬሽን | 4000 | 1,163,810,101.29 | 495,561,698.98 | 43% | 77.10% |
| 7 | አጅማ ጫጫ ፕሮጀክት ሎት3 | አማራ.ውሃ ሥራዎች ኮርፖሬሽን | 3000 | 1,480,395,150.20 | 304,815,396.21 | 21% | 81.20% |
| 8 | ወይቦ መስኖ ግብባታ ሎት2 | ክሮስላንድ ኮንስትራክሽን ጂቪ OCC | 1800 | 1,248,412,635.12 | 40,934,056.66 | 3% | 8.20% |
| | **አማካይ** | | | | **337,398,437.48** | **36%** | **61.4%** |

**3%** ወይም ብር 40,934,056.70 የዋጋ ማስተካከያ የተደረገበት መሆኑን ያመላክታል፡፡ በናሙና ከታዩት ስምንት (8) ፕሮጀክቶች ውስጥ የፕሮጀክቶች የሥራ አፈጻጸም በአማካይ **61.4%** ሲሆን፣ የዋጋ ማስተካከያ የተደረገው በአማካይ **36%** ነው፡፡ ይህም ከ8ቱ ፕሮጀክቶች ውስጥ ከአማካይ የዋጋ ማስተካከያ በላይ የተደረገላቸው 5 ፕሮጀክቶች ከ43%--65.9% መሆናቸውን ጥናቱ ያሳያል፡፡ ይህም መንግስት ካስቀመጠው የግዥ ህግ 25% በላይ መሆኑን ያመለክታል፡፡

የዋጋ ጭማሪ የተደረገው በመጀመሪያ በግዥ አፈጻጸም ጊዜ የተቀመጠ ስምምነት ወይም መስፈርት በሌለበት ሲሆን፣ በግንባታ ውሉ ውስጥ በርካታ ውሎች የዋጋ ማስተካከያ የለም በሚል ከተስማሙ በኋላ እና በተለያዩ ጊዜ የጊዜ ማራዘሚያ ተደርጎ በወቅቱ ባልተጠናቀቀበት ከመሆኑ በተጨማሪ የዋጋ ማስተካከያው የጊዜም ሆነ የገንዘብ ገደብ እንዳይኖረው ማድረግ ለጥቅም ግጭት በሚዳርግ ሁኔታ እየተተገበረ በመሆኑ መንግስት በዋጋ ማስተካከያ አላስፈላጊ ከፍተኛ ወጪ እንዲያወጣ አድርጎታል፡፡

**የዋጋ ማስተካከያ ቀመር ማባዣ(factors) የሚያሳይ ሠንጠረዥ ቁጥር 06፣**

| ተ.ቁ | የፕሮጀክቱ ሥም | የዋጋ ማስተካከያ ፋክተሮች መነሻ | | መረጃው ሲሰበሰብ የነበረው የዋጋ ማስተካከያ መጠን | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | በመቶኛ | በቁጥር | በመቶኛ | በቁጥር |
| 1 | ጨል-ጨል ሎት--1 ፕሮጀክት | 60% | 0.6 | 173% | 1.73 |
| 2 | ጨል-ጨል ሎት--2 ፕሮጀክት | 60% | 0.6 | 321% | 3.21 |
| 3 | ቄጦ የአናት ሥራ ፕሮጀክት | 60% | 0.6 | 294% | 2.94 |
| | **አማካይ** | | | **263%** | **2.63** |

ምንጭ፡- ከመስኖ እና ቆላማ አካባቢ ሚ/ር እና ከአጥኝ ቡድን ስሌት

ከላይ በሰንጠረዡ እንደሚታየው የዋጋ ማስተካከያ ማባዣዎች (Factors) ከ0.6 ወደ 3.21 የደረሰ መሆኑን መረጃው ያሳያል፡፡ ይህ ዓይነት የዋጋ ማስተካከያ ማባዣዎች በሚዘጋጀው የክፍያ ሰነድ ወይም በየወሩ እየጨመረ የሚሄድ ሲሆን፣ የሚጨምረውም የዋጋ ልዩነት የጊዜ ቀመር እየጨመረ እንደሚሄድ ለማወቅ ተችሏል፡፡ ሥራው እስኪያልቅ ወይም እስኪጠናቀቅ ድረስ እየጨመረ የሚሄድ እንጂ የሚያቆመው ነገር አለመኖር የዋጋ ማስተካከያው በሎት እንጂ በፕሮጀክት አፈጻጸም ደረጃ አለመሆኑ፣ መንግስት ከፍተኛ የዋጋ ማስተካከያ ወጪ እንዲያወጣ የሚያደርግ ስለሆነ የፕሮጀክት ዋጋ ማስተካከያ ለሀብት ብክነት የተጋለጠ ሆኖ ይታያል፡፡

## 3.9. የንጥል ጥናት ትንተና ውጤት (Case study Results)

### 3.9.1.የመገጭ ግድብ ግንባታ እና የመስኖ ልማት ፕሮጀክት ተያያዥ ስራዎች ፣

#### 3.9.1.1.የመገጭ ግድብ ግንባታ ፕሮጀክት ያለበት ደረጃ፣

የመገጭ ግድብ ፕሮጀክት በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በሰሜን ጎንደር ዞን በጎንደር ዙሪያ ወረዳ ይገኛል፡፡ በመገጭ ወንዝ አዋሳኝ በመሆኑ በአካባቢው የሚገኙ አርሶ አደሮችን የምግብ ዋስትና ማረጋገጥና ለሀገሪቱ ኢኮኖሚ እድገት የበኩለን አስተዋጽኦ ከማበርከት አኳያ እስከ 17,000 ሄክታር የመስኖ እርሻ የማልማት አቅም አለው፡፡ በተጨማሪም በጎንደር ከተማ እና በጎንደር ዙሪያ በሚገኙ ከተሞች ለሚኖረው ህብረተሰብ የንፁህ መጠጥ ውሃ አገልግሎት ማቅረብ የሚቸል ነው፡፡

በፕሮጀክት ውል ስምምነቱ መሰረት የሚሰሩ ዋና ዋና ሥራዎች፡- ዋና ግድብ (Main Dam)፣ ካዝና ግድብ (Coffer Dam)፣ የውሃ ማስተንፈሻ (Spill way)፣ የቀኝ ውሃ ማስወጫ (Right Intake)፣ የግራ ውሃ ማስወጫ(Left Intake)፣ ማስገቢያ ማማ (Intake Tower)፣ መሳሪያ (Instrementation)፣ ሃይደሮ መካኒካል (Hydro Mechanical)፣ ኤሌክትሪካል (Electrical)፣ የመንገድ መዳረሻ ግንባታ (Access to Road Construction) ሥራዎች ናቸው፡፡

### 3.9.1.2. የግንባታ ግዥ አፈጻጸም ግልጽነት፣

የመገጭ ፕሮጀክት የአዋጭነት እና የአካባቢ ተፅኖ ጥናት ተካሂዷል፡፡ የመጀመሪያው የመገጭ ግድብ ግንባታ ፕሮጀክት ሥራ በዓለም አቀፍ የጨረታ ውድድር ግዥው የተፈፀመ ነው፡፡ የመጀመሪያው የመገጭ ግድብ ግንባታ ፕሮጀክት ስምምነት የተፈረመው በመስከረም 2001 ዓ.ም ቢሆንም፣ ሥራ የጀመረው ግን ከ4 ዓመት በኋላ በጋቢት 2005 ዓ.ም ነው፡፡ ለፕሮጀክቱ የተሰጠው የማጠናቀቂያ ጊዜ 48 ወራት ነው፡፡ የመጀመሪያው የመገጭ ግድብ የግዥ ሠነድ መረጃ በሚ/ር መ/ቤቱ አልተገኘም፡፡

የመጀመሪያው የፕሮጀክቱ ተቋራጭ የውሃ ስራዎች ኮንስትራቸሽን ድርጅት ነው፡፡ የመገጭ ግድብ ግንባታ ፕሮጀክት ውል ከተቋራጩ ጋር የነበረው ስምምነት የተቋረጠው ግንቦት 07/2016 ዓ.ም ነው፡፡ በ2016 በጀት ዓመት መጨረሻ በአጠቃላይ በግድቡ እና ተያያዥ ሥራዎች ግንባታው የደረሰበት ደረጃ 66 % ነው፡፡ ይህ ተቋራጭ ሲሰራው የነበረው የግድብ ፕሮጀክት ሥራ 66 በመቶው ከተጠናቀቀ በኃላ ተቋርጦ ሌላ አዲስ ተቋራጭ ቀሪውን 34 በመቶ ሥራ ለመስራት በመስኖ እና ቆላማ አካባቢ ሚ/ር እና ቤ.አ.ኤ.ካ ጠቅላላ ንግድ ሥራ ድርጅት መካከል በቀጥታ ግዥ በቀን 14/09/2016 ዓ.ም ስምምነት ተፈፅሟል፡፡ የ34 በመቶ ፕሮጀክት ሥራው ዋጋ ብር 14,238,910,585.61 ነው፡፡ ይህ በ14/09/2016 ዓ.ም የተቋራጭ ግዥ እንዲካሄድ የተፈቀደው ግዥ የተፈፀመው የማህንዲስ ግምት (የEngineering estimation) ሳይሰራለት በቀጥታ በዋጋ ድርድር የተሰጠ ነው፡፡ የውል ስምምነቱ በሚ/ር መ/ቤቱ እና ቤ.አ.ኤ.ካ ጠቅላላ ንግድ ሥራ መካከል ሰኔ 09/2016 ዓ.ም ተፈርሟል፡፡

### 3.10.1.3. የፕሮጀክቱ የውል ጊዜ እና የዋጋ ስምምነቶች ግልጽነት በተመለከተ፣

የመገጭ ፕሮጀክት የውል ስምምነት በውሃ ሀብት ሚ/ር እና በውሃ ስራዎች ኮንስትራቸሽን ድርጅት መካከል መስከረም 2001 ዓ.ም ተፈራረሙ፡፡ 6ኛው የውል ማሻሻያ የተደረገበት ዋጋ የማህንዲስ ግምት (የኢንጂነሪከግ እስቲሜሽን) ሳይሰራለት በቀጥታ በድርድር የተሰጠ ነው፡፡ በ14/09/2016 ዓ.ም የተቋራጭ ግዥ እንዲካሄድ የተፈቀደ መሆኑ የተገለፀ ቢሆንም የመንግስት ግዥ ኤጀንሲ የፈቀደበት ደብዳቤ ግን በሰነዱ ማግኘት አልተቻለም፡፡ በአዲሱ ውል መሰረት የፕሮጀክቱ የውል ማጠቃቂያ ጊዜው ሁለት (2) ዓመት ወይም እስከ ሰኔ 08/2018 ዓ.ም ነው፡፡

ለአማካሪው (ለኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ዲዛይንና ሱፐርቪዥን ሥራዎች ከርፖሬሽን) የአሁኑ ወሃ እና ኢነርጂ ዲዛይንና ሱፐርቪዥን ሥራዎች ድርጅት የ9ኛው የጊዜ ማራዘሚያ የተፈራረመው መጋቢት 26/2013 ዓ.ም ነው፡፡ የውል ጊዜ ማራዘሚያ የተሰጠው ደግሞ ከሰኔ 24/202013 አስከ ሰኔ 23/2016 ለ36 ወራት ነበር፡፡ በዚህ የጊዜ ማራዘሚያ ሚ/ር መ/ቤቱ እና አማካሪው የተስማሙት ክፍያ 84,099,364.45 ብር ነው፡፡

### 3.9.1.4. የመገጭ ግድብ ግንባታ ፕሮጀክት የውል ጊዜ እና የዋጋ ማሻሻያዎች ግልጽነት፣

የመገጭ ግድብ ግንባታ ፕሮጀክት እስከ ሰኔ 22/2016 ዓ.ም ድረስ ለ6 ጊዜ የጊዜ ማራዘሚያ ተሰጥቶታል፡፡ የፕሮጀክቱ ሥራ የመነሻ ዋጋ መጠን ተ.እ.ታን ጨምሮ በብር 2,451,953,789.00 ነበር፡፡ 6ኛው የፕሮጀክት የውል ማሻሻያ መጠን ተ.እ.ታ.ጨምሮ ብር 6,434,127,429.00 ነው፡፡ እስከ ዚህ ጊዜ ድረስ መንግስት በግድብ ግንባታው 3,982,173,640.00 ብር ተጨማሪ ወጪ እንዲያወጣ አድርጎታል፡፡ የመገጭ ግድብ ግንባታ ፕሮጀክት ለ6 ጊዜ የውል ማሻሻያ ተደርጓል፡፡

**የውል ማሻሻያ ቁጥር1** (የመጀመሪያው የውል ማሻሻያ) የተደረገው የካቲት 15/2005 ዓ.ም ነው፡፡ የውል ማሻሻያ የተደረገው በበጀት እጥረት ምክንያት ሥራው ሳይጀመር ለ4 ዓመት በመዘግየቱ እንደሆነ መረጃው ያሳያል፡፡

**የውል ማሻሻያ ቁጥር ሁለት (2)** የተደረገው የካቲት 19/2007 ዓ.ም ነው፡፡ የውል ማሻሻያ የተደረገበት ምክንያት ኮንትራክተሩ የነጠላ ዋጋ እንዲሻሻልለት በመጠየቁ ነው፡፡ በውል ማሻሻያ ቁጥር 2 መሰረት የፕሮጀክቱ ጠቅላላ መነሻ ዋጋ 5,654,431,490.95 ብር እንዲሆን ተደርጓል፡፡ በዚህ የውል ማሻሻያ ቁጥር ሁለት መሰረት የመነሻ ዋጋውን 20 በመቶ ለኮንትራክተሩ እንዲከፈለው ተደርጓል፡፡ ለፕሮጀክቱ የዋጋ ማሻሻያም የተደረገለት **14,361,746.99** ብር ተደርጓል፡፡

**የውል ማሻሻያ ቁጥር ሶስት (3)**፡- የፕሮጀክቱ የውል ማሻሻያ የተደረገው በውሃ፣ መስኖ እና ኤሌክትሪክ ሚ/ር እና በኢትዮጵያ ውሃ ሥራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት መካከል ግንቦት 03/2008 ዓ.ም ነው፡፡ ውሉ የተሻሻለበት ምክንያት በፕሮጀክቱ ወሰን ውስጥ ያሉ ሥራዎች ላይ መጨመር እና መቀነስ (Addition and Omission) በማስፈለጉ ነው፡፡ በዚህም የውል ማሻሻያ ቁጥር 3 የፕሮጀክቱ መነሻ ዋጋ 5,667,130,760.53 ብር እንዲሆን ተደርጓል፡፡ ይህም ከውል ማሻሻያ ቁጥር 2 ላይ የተቀነሰው 568,308,636.31 ሲሆን የተጨመረው ግን 661,081,436.25 ነው፡፡ ከውል ማሻሻያ ቁጥር 2 ላይ ለውል ማሻሻያ ቁጥር 3 የተቀነሰው እና የተጨመረው ሲታይ ልዩነቱ 92,772,799.94 ብር ተጨማሪ ሥራ ለኮንትራክተሩ እንዲሰጥ ተደርጓል፡፡ የፕሮጀክቱ የዋጋ ማስተካከያ ደግሞ **14,361,746.99** ብር ተደርጓል፡፡

**የውል ማሻሻያ ቁጥር አራት(4)**፡- የውል ማሻሻያ ቁጥር 4 የተደረገው በመስኖ ልማት ኮመሽን እና በኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ሥራዎች ኮርፖሬሽን መካከል ጥር 2012 ዓ.ም ነው፡፡ የውል ማሻሻያ የተደረገበት ምክንያት አዳዲስ ዝርዝር ሥራዎች በመጨመራቸው፣ በተወሰኑ እቃዎች ላይ መቀነስ እና መጨመር በማሸፈለጉ፣ የዲዛይን ለውጥ በመደረጉ፣ በውሃ ማፋሰሻው መሰረታዊ ለውጥ በመኖራቸው ነው፡፡ የውል ማሻሻያ ቁጥር 4 መነሻ ዋጋ 5,931,042,722.42 ብር ነው፡፡ በውል ማሻሻያ ቁጥር 4 ለተጨመሩ ሥራዎች የተያዘው በጀት 679,026,557.32 ብር ሲሆን ለቀሪ ሥራዎች የተቀነሰው ገንዘብ ደግሞ 424,756,610.53 ብር እንዲሆን ተደርጓል፡፡ ልዩነቱ 25,4271,946.79 ብር ነው፡፡

የዋጋ ማሻሻያ የተሰጠው **14,361,746.99** ብር በተመሳሳይ (Constant),ሁኔታ ነው::

**የውል ማሻሻያ ቁጥር አምስት (5)** የተደረገው በመስኖ ልማት ኮሚሽን እና በኢትዮጵያ ውሃ ሥራዎች ኮርፖሬሽን መካከል ጥር 25/2014 ዓ.ም ነው፡፡ ውሉ የተሻሻለበት ምክንያት የቅድሚያ ክፍያው ሞዳሊቲ **ከ20 በመቶ ወደ 30 በመቶ** ከፍ ለማድረግ ነው፡፡ በዚህም የውል ማሻሻያው ቁጥር 5 መነሻ ዋጋው 5,931,042,722.42 ብር ነው፡፡ የዚህ ውል የማጠናቀቂያ ጊዜ ሰኔ 27/2014 ዓ.ም ነው፡፡

በውል ማሻሻያው ቁጥር 5 የተጨመረው ሥራ ዋጋ 1,064,608,275.28 ሲሆን የተቀነሰው ሥራ ደግሞ 549,997,153.1 ብር ነው፡፡ የተጨመረው ሥራ ከተቀነሰው ሥራ ያለው የወጪ ልዩነት 514,629,122.18 ብር ነው፡፡

**የውል ማሻሻያ ቁጥር 6** የመገጭ ግድብ ግንባታ በመስኖ እና ቆላማ አካባቢ ሚ/ር እና በኢትዮጵያ ኮንስትራክሽን ሥራዎች ኮርፖሬሽን መካከል ሰኔ 9/2014 ዓ.ም ተፈርሟል፡፡ የውል ማሻሻያው መነሻ ዋጋ 6,434,127,429.82 ብር ነው፡፡ የውል ማጠናቀቂያ ጊዜው እስከ ሰኔ 22/2017 ዓ.ም እንዲሆን ተደርጓል፡፡

### 3.9.1.5. የመገጭ ግድብ ግንባታ ፕሮጀክት የውል መቋረጥ ግልጽነት፣

የመገጭ ግድብ ግንባታ ፕሮጀክት ውል ከተቋራጩ ጋር የተቋረጠው ግንቦት 07/2016 ዓ.ም ነው፡፡ ውሉ በተቋረጠበት ጊዜ የፕሮጀክቱ ሥራ አፈጻጸም የደረሰበት ደረጃ 66 በመቶ ነው፡፡ ፕሮጀክቱ ከ2013 ዓ.ም በፊት አፈጻጸሙ ከ75 በመቶ በላይ ደርሶ ነበር፡፡ ነገር ግን በ2013 ዓ.ም የግድቡ ማዕከላዊ ክፍል የመሰንጠቅ አደጋ ደረሰበት፡፡ በ2014 ዓ.ም የተሰነጠቀውን ግድብ መጠገን አልተቻለም፡፡

በ2015 ዓ.ም ይህ የግድቡ ማዕከላዊ ክፍል የመፍረስ አደጋ ደረሰበት፡፡ በዚህ ምክንያት በሚ/ር መ/ቤቱ እና በኮንትራክተሩ መካከል የነበረው ውል እንዲቋረጥ ተደረጓል፡፡

የግድቡ ማዕከላዊ ክፍል መፍረስ ምክንያት የሆነው የሥራው ቅደም ተከተል (work procedure) አለመጠበቅ እና የስልት (methiodology) ችግር መሆኑ ታውቋል፡፡ ይህ የተፈጠረው በተቋራጩ ግድየለሽነት ምክንያት የተከሰተ ነው ተብሏል፡፡ የፕሮጀክቱ በጊዜ አለመጠናቀቅ ምክንያቱ በኮንትራክተሩ ደካማ አፈጻጸም ቢሆንም ኮንትራክተሩ ግን ያለምንም ቅጣት በአሚኬብል (win-win) ስምምነት ተቋርጦ  የተሰናበተ መሆኑን ያመለክታል፡፡ ለፕሮጀክቱ መቋረጥ፣ ለተጨማሪ ጊዜም ሆነ ወጪ ተጠያቂ የሆነ ተቋራጭም ሆነ አማካሪ የለም፡፡

ውሉ ከኮንትራክተሩ ጋር በተቋረጠበት ወቅት ለተቋራጩ በጠቅላላው 1,472,670,082.68 ብር ቅድሚያ ክፍያ የተከፈለው ሲሆን፣ ከዚህ ውስጥ  ተመላሽ የተደረገው 908,794,113.38 ብር ነው፡፡  እንዲሁም 32,706,338.80 ብር ለዋጋ ማስተካከያ ክፍያ ተከፍሎታል፡፡

የመገጭ ግድብ ግንባታ እና የመስኖ ልማት ፕሮጀክት የነበረው ኮንትራክተር ተቀይሮ ለአዲሱ ቤ.አ.ኤ.ካ ጠቅላላ ንግድ ሥራ ተቋራጭ በ14,238,910,585.61 ብር ተሰጥቶታል፡፡ የፕሮጀክት ሥራው የተሰጠው በቀጥታ የግዥ ዘዴ ሲሆን፣ የውል ስምምነቱ በመስኖ እና ቆላማ አካባቢ ሚ/ር መ/ቤት እና ቤ.አ.ኤ.ካ ጠቅላላ ንግድ ሥራ መካከል ሰኔ 09/2016 ዓ.ም ተፈርሟል፡፡  የፕሮጀክት የውል ማጠቃቂያ ጊዜው 24 ወራት ወይም 2 ዓመት ነው::

በአጠቃላይ የመገጭ ግድብ ግንባታ ፕሮጀክት አለመጠናቀቅ እንደ ምክንያት የቀረቡ ጉዳዩች፡- የወሰን ማስከበር (የካሳ ክፍያ ችግር)፣ የተቋራጩ የፋይናንስ አቅም መድከም፣ የግድቡ ግንባታ  መፍረስ (የጥራት ጉድለት) እና የአማካሪው የአቅም ድክመት መሆኑ ተከልፃል፡፡

### 3.9.2. አርጆ ዲዴሳ ግድብና መስኖ ልማት ፕሮጀክት ያለበት ደረጃ

#### 3.9.2.1. የአርጆ ዲዴሳ ግድብ ፕሮጀክት ያለበት ደረጃ፣

የአርጆ ዴዳሳ መስኖ ግዴብ ግንባታ ፕሮጀክት በኦሮሚያ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት በቡኖ በደሌ፣ ምስራቅ ወለጋ እና ጂማ ዞን የሚዋሰኑበት ስፍራ የሚገኝ ሲሆን ሲጠናቀቅ 80,000 ሄ/ር የማልማት ከፍተኛ አቅም ያለው ፕሮጀክት ነው፡፡ አጠቃላ የፕሮጀክቱን የግድብ እና ተጓዳኝ ስራዎች ግንባታ በ2016 በጀት ዓመት መጨረሻ በአማካይ 71% ነው፡፡ የአርጆ ዲዴሳ ፕሮጀክት አንድ የሥራ አካል የሆነው ፕሮጀክት የውሃ ማስተንፈሻ እና የቀኝ ውሃ ማስወጪያ (Spill way and Right Intake Structures) ግንባታ  በ2016 የበጀት ዓመት መጨረሻ 22.1% ማድረስ ተችሏል፡፡ የሰፋሪዎች የመሠረተ ልማት ግንባታ ሥራ በ2016 በጀት ዓመት 96.41% የደረሰ ሲሆን፣  እንዲሁም የዋናዉ ግድብ እና የኮሪዶ ግንባታ ስራዎች (ሎት-1) ግንባታ በ2016 የበጀት ዓመት መጨረሻ 94.5% የደረሰ መሆኑን መረጃዎች ያሳያሉ::

## 3.9.2.2. የአርጆ ዲዴሳ ግድብ ግንታ ግዥ አፈጻጸም ግልጽነት፣

የአርጆ ዲዴሳ ግድብ ፕሮጀክት እና ተጓዳይ ሥራዎች ፕሮጀክት የአዋጭነት እና የአካባቢ ተፅዕኖ ጥናት የተካሄደ ሲሆን፣ አማካሪው እና የሥራ ተቋራጩ ጨረታ የተወዳደሩበት የዲዛይንም፣  የሱፐርቪዥን እና የሥራ ተቋራጩ ግዥ አፈጻጸም ሰነዶች  በሚ/ር መ/ቤቱ

አልተገኘም፡፡ የአርጆ ደዴሳ ፕሮጀክት ሥራውን ለመስራት ውል በመዋዋል እየሰሩ ያሉት በውሃና ኢነርጂ ሚ/ር እና በኦሮሚያ ውሃ ሥራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት መካከል ነው፡፡ አማካሪውም ደግሞ ኦሮሚያ ውሃ ስራዎች ዲዛይን ድርጅት ነው፡፡

### 3.9.2.3. የአርጆ ዲዴሳ ግድብ ግንባታ እና ተያያዥ ፕሮጀክቶች የውል ስምምነቶች ግልጽነት፣

በውሃና ኢነርጂ ሚ/ር እና በኦሮሚያ ውሃ ሥራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት መካከል ጥር 23/05/2003 ዓ.ም ውል ተዋውለዋል፡፡ የአርጆ ዲዴሳ ግድብ ግንባታ እና ተያያዥ ሥራዎች ፕሮጀክት የመጀመሪያ ሥራ የጀመረው የካቲት/ 2003 ዓ.ም ነው፡፡ የአርጆ ዲዴሳ የመጀመሪያው የፕሮጀክት ዋጋ 755,461,980.84 ብር ነው፡፡ በውሉ መሰረት የመጀመሪያው የፕሮጀክቱ ሥራ ማጠናቀቂያ ጊዜ 18 ወራት ነው፡፡

ከአማካሪው ጋር በተደረገው ውል ለ8 ጊዜ ማሻሻያ ተደርጓል፡፡ ከተቋራጩ ጋር ደግሞ ለ6 ጊዜ እንዲሁም ለ4 ጊዜ የዋጋ ማስተካከያ ስምምነት ተደርጓል፡፡ ለ6ኛ ጊዜ የተሻሻለው የአርጆ ዲዴሳ ግድብ እና ተጓዳይ ሥራዎች ፕሮጀክት ዋጋ ብር 7,551,044,817.93 ደርሷል፡፡ ይህ ፕሮጀክት የሚጠናቀቅበት ቀን ግንቦት 23/2017 ዓ.ም ነው፡፡ አፈጻጸሙ በ2016ዓ.ም መጨረሻ በአማካይ 71% ነው፡፡

የአርጆ ዲዴሳ ግድብና ተጓዳኝ ሥራዎች ፕሮጀክት የውል ስምምነት ያካተታቸው ሥራዎች፡- የመዳረሻ መንገዶች ግንባታ፣ የዋና ግድብ ግንባታ፣ የኮርቻ ግድብ ግንባታ፣ የማስቀየሻ ግድብ ግንባታ፣ የውሃ ማስተንፈሻ፣ የቀኝ እና የግራ ውሃ ማስወጫ እና የግድቡ መሰረት ማሻሻያ (Grouting) ግንባታ ናቸው፡፡ ይሁን እንጂ የቀኝ እና የግራ ውሃ ማስወጫ፣ የውሃ ማስተንፈሻው ግንባታ እና የግድቡ መሰረት (pile foundation) ማሻሻያ ከመጀመሪያው የአርጆ ዲዴሳ ግንባታ ውስጥ እንዲወጡ ተደርጓል፡፡ በዚህ መሰረት የመጀመሪያው የአርጆ ዲዴሳ የውሃ ማስተንፈሻና የቀኝ ውሃ ማስወጪያ ግንባታ ውል ስምምነት በአዲስ መልክ በመስኖ እና ቆላማ አካባቢ ሚ/ር እና በኦሮሚያ ኮንስትራክሽን ኮርፖሬሽን (ተቋራጭ) መካከል የተፈራረሙት ግንቦት 15/2016 ዓ.ም ነው፡፡ አማካሪው ደግሞ የዋናው ፕሮጀክት አማካሪ የኦሮሚያ ውሃ ስራዎች ዲዛይን ድርጅት ነው፡፡

ከዋናው ግድብ ተቀንሶ እና ራሱን ችሎ እንዲገነባ የተደረገው የውሃ ማስተንፈሻ እና የቀኝ ውሃ ማስወጫ (Spillway and Right Intake Structures) ግንባታ የመነሻ ዋጋ 2,646,000,522.45 ብር ነው፡፡ በውሉ መሰረት ፕሮጀክቱ የማጠናቀቂያ ጊዜ 24 ወራት ነው፡፡ ይህ ፕሮጀክት በ2016 በጀት ዓመት መጨረሻ የደረሰበት ደረጃ 22 በመቶ ነው፡፡

### 3.9.2.4. የአርጆ ዲዴሳ ፕሮጀክት የውል ማሻሻያዎች አፈጻጸም ግልጽነት፣

የውሃ ማስተንፈሻ እና የቀኝ ውሃ ማስወጪያ (Spillway and Right Intake Structures) ግንባታ የመጀመሪያ ቦታውን በመቀየሩ እና ሌላ ተጨማሪ ሥራ በማምጣቱ ምክንያት የውል ማሻሻያ ተደርጓል፡፡ የተሻሻለው የውሃ ማስተንፈሻና የቀኝ ውሃ ማስወጪያ ውል የተፈረመው መስከረም 2015 ዓ.ም ነው፡፡ ለተጨማሪ ሥራዎች የዋጋ ማስተካከያ የተደረገው 1,050,114,858.97 ብር ነው፡፡ የተሸሻለው የውሃ ማስተንፈሻና የቀኝ ውሃ ማስወጪያ ግንባታ እና የተጨማሪ ሥራዎች የውል ማሻሻያ የተደረገው ጠቅላላ ዋጋ 3,181,322,733.30 ብር ሆኗል፡፡

የመጀመሪያው የአርጆ ዲዴሳ ግድብ ግንባታ ፕሮጀክት የዲዛይን ክለሳ ተደርጎለታል፡፡ በዚህ ውስጥ የውሃ ማስተንፈሻው (Spill way) ሙሉ በሙሉ ከመጀመሪያ ቦታው ተቀይሯል፡፡ እንዲሁም የኮርቻ ግድብ 1 (አንድ) ዲዛይን በመቀየሩ ተጨማሪ ሥራ እንዲመጣ አድርጓል፡፡ ከመጀመሪያ የውል ስምምነት የሥራ መጠን መጨመር የዲዛይን ማሻሻያ እንዲመጣ አድርጎታል፡፡ በመሆኑም ዲዛይኑ እና ፕሮጀክቱ እንዲከለስ ሆኗል፡፡

የዲዛይኑ መከለስ ምክንያት የሆነው የፕሮጀክቱ መነሻ ሲጀመር የሥራ ዝርዝር መጠን እና የወጪ ግምት መጠን በአግባቡ የተገናዘበ አለመሆን፣ የግድቡ አካል የሆኑ ሥራዎችን አለማካተት፣ በመነሻ ውሉ ስምምነት ጊዜ የነጠላ ዋጋ ያስቀመጡት በኮሚቴ እንጂ በባለሙያና የገበያ ዋጋን ግምት ውስጥ ያስገባ አለመሆኑን ከሰነዶች የተገኘው መረጃ ያሳያል፡፡

የመጀመሪያው የውል ስምምነት ወደ ውል ቁጥር 01 እንዲሻሻል መነሻ ምክንያቶች ውስጥ፡- ለፕሮጀክቱ የተሰጠው የማጠናቀቂያ ጊዜ ግምት ዝቅተኛ መሆን፣ ነጠላ ዋጋ ያልተቀመጠላቸው ዝርዝር ሥራዎች መኖር ናቸው፡፡

**የውል ማሻሻያ ቁጥር 01**

የአርጆ ዲዴሳ ፕሮጀክት የመጀመሪያው የውል ማሻሻያ ቁጥር 01 ታህሳስ 17/2003 ዓ.ም በብር 1,2989,19,272.91 ተፈራረሙ፡፡ የውል ማሻሻያ ቁጥር 01 ማጠናቀቂያ ጊዜ ከ18 ወራት ወደ 42 ወራት ከፍ እንዲል ተደርጓል፡፡ የተሻሻለው ውል ተጨማሪ ማጠናቀቂያ ጊዜ 24 ወራት ሆኖ ተቀምጧል፡፡

**የውል ማሻሻያ ቁጥር 01** ስምምነት በሚተገበርበት ጊዜ ተቋራጩ (የኦሮሚያ ውሃ ሥራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት) የነጠላ ዋጋ ሬት እንዲሻሻልለት በቀን 23/08/2007 ዓ›ም ለፕሮጀክቱ ባለቤት (ለውሃ፣ መስኖ እና ኤሌክትሪክ ሚ/ር) ጥያቄ አቅርቧል፡፡ ይህም የውል ማሻሻያ ቁጥር 01 የተወሰነው የነጠላ ዋጋ ዝቅተኛ በመሆኑ በተቋራጩ አማካኝነት የውል ማሻሻያ ቁጥር 02 ማሻሻያ እንዲደረግ ጠየቀ፡፡ ምክንያቱ ደግሞ የተቋራጩን የፋይናንስ ኪሳራ ያላገናዘበ በመሆኑ ነው የሚል ነው፡፡

በዚህ መሰረት የፕሮጀክቱ አማካሪ (የኦሮሚያ ውሃ ሥራዎች ዲዛይን እና ሱፐርቪዥን ድርጅት) የውል ማሻሻያ ፕሮፖዛል በማዘጋጀት የውል ማሻሻያ ቁጥር **02** ለባለቤቱ በቀን 18/01/2008 ዓ.ም አቅርቧል፡፡ የፕሮጀክቱ ባለቤት የቀረበው ፕሮፖዛል እንዲፀድቅለት ለፋይናንስ እና ኢኮኖሚ ሚ/ር በቀን 03/01/2008 ዓ.ም ደብዳቤ የጻፈ መሆኑን መረጃው ያሣያል፡፡ የገንዘብና ኢኮኖሚ ሚ/ር ደግሞ ፕሮፖዛሉን ያፀደቀው መሆኑን በቀን 29/03/2008 ዓ.ም ለውሃ፣ መስኖና ኤሌክትሪክ ሚ/ር ጽፎለታል፡፡

በዚህ መሰረት **የውል ማሻሻያ ቁጥር 02** በውሃ፣ መስኖ እና ኤሌክትሪክ ሚ/ር እና በኦሮሚያ ውሃ ሥራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት መካከል ታህሳስ 07/2008 ዓ.ም በተሻሻለው ፕሮጀክት ዋጋ ተ.እ.ታ.ጨምሮ ብር 2,594,716,574.30 ተፈራረሙ፡፡ የፕሮጀክቱ ማጠናቀቂያ ጊዜ 78 ወራት ሲሆን፣ ለውል ማሻሻያ ቁጥር 02 የተሰጠው ተጨማሪ የማጠናቀቂያ ጊዜ 36 ወራት ወይም 3 ዓመት ነው፡፡

የውል ማሻሻያ ቁጥር 02 በሚተገበርበት ጊዜ ተጨማሪ የዲዛይን ማሻሻያ ተደርጓል፡፡ ምክንያቱ በ2007 ዓ.ም ክረምት **በውሃ ማጠራቀሚያ ማስቀየሻው** (የኮርቻ ግድብ) ላይ የጎርፍ አደጋ በማጋጠሙ ነው፡፡ የዲዛይን ማሻሻያው የግድቡን ቁመት በ 3 ሜትር ከፍታ እንዲጨምር በመደረጉ የተጓዳይ ሥራዎች መጠን እንዲጨምር አድርጎታል፡፡ በዚህም ምክንያት የፕሮጀክቱ ባለቤት የተጓዳኝ ሥራዎች እንዲቀነሱ ወሰነ፡፡ እነሱም፡- የውሃ ማስተንፈሻውን፣ የቀኝና የግራ ውሃ ማስዎጫዎችን፣ እና ሀይድሮ ሜካኒካል መሳሪያዎችን ከውል ማሻሻያ ቁጥር 02 እንዲወጡ ተደረጉ፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ ተቋራጩ የፋይን ፊልተርና የክለይ ማቴሪያል እና የኳየሪ ሳይት እርቀት ልዩነት በመምጣቱ ምክንያት የነጠላ ዋጋ ክለሳ (ማሻሻያ) እንዲደረግለት ጠየቀ፡፡

ሌላው በፕሮጀክቱ ባለቤት እና በተቋራጩ መካከል መግባባት በመፍጠር የዛፍ እና የደን ምንጣሮ ወደ ግድቡ እና ተጓዳይ ሥራዎች እንዲካተት አደረጉ፡፡ ከዚያም አማካሪው የኦሮሚያ ውሃ ሥራዎች ዲዛይን እና ሱፐርቪዥን ድርጅት የውል ማሻሻያ ቁጥር 03 ለባለቤቱ አዘጋጅቶ እኒዲያፀድቅለት በቀን 09/4/2010 ዓ.ም አቅርቧል፡፡

በመሆኑም የውል ማሻሻያ ቁጥር 03 በውሃ፣ መስኖ እና ኤሌክትሪክ ሚ/ር እና በኦሮሚያ ውሃ ሥራዎች ድርጅት መካከል ሚያዚያ 12/2010 ዓ.ም በፕሮጀክት ማሻሻያው ዋጋ መጠን ተ.እ.ታ ጨምሮ በብር 290,8787,140.70 ተፈራረሙ፡፡ የውል ማሻሻያ ፕሮጀክት ማጠናቀቂያ ጊዜ 102 ወራት ሲሆን፣ እስከ 8/2011 ዓ.ም እንዲጠናቀቅ ተስማምተው ተፈራረሙ፡፡ የማሻሻያ ቁጥር 03 ፕሮጀክቱ የማጠናቀቂያ ጊዜ 24 ወራት ተሰጥቶታል፡፡

**የውል ማሻሻያ ቁጥር 04 የተሻሻለበት ምክንያት፣**

በአጠቃላይ የፕሮጀክቱ አፈጻጸም እንዲዘገይ ከአደረጉት ምክንያቶች አንዱ የካሳ ክፍያ መዘግየት ነው፡፡ ይህም በውሃ ማጠራቀሚያው አካባቢ የሚኖሩ ሰዎች፣ ዛፎች እና ሌሎች ሜካዎች በኮርቻ ግድቡ አካባቢ መንቀሳቀስ አለመቻል ነው፡፡ፕሮጀክቱ በተለያዩ ምክንያቶች የዘገየ ቢሆንም የአፈጻጸም ደረጃው ግን 2011 ዓ.ም 70.90 በመቶ ደርሷል፡፡ ተቋራጩ ቀሪ 29.10 በመቶ ሥራዎችን ለማጠናቀቅ 360 ቀናት የጊዜ ማራዘሚያ (ከሐምሌ 01/2011 እስከ ሰኔ 30/2012) ጠይቋል፡፡ አማካሪው ሥራው የዘገየበትን ሁኔታ ከገመገመ በኋላ የተቋራጩ የጊዜ ማራዘሚያ እንዲጸድቅ ፕሮፖዛሉን ለባለቤቱ አቅርቧል፡፡

የኮርቻ ግድብ ዲዛይን ከነበረበት ቦታ በመቀየሩ ምክንያት የውሃ ማስተንፈሻውም በሌላ ቦታ እንዲቀየስ ተደርጓል፡፡ የውሃ ማስተንፈሻ እና የቀኘ ውሃ ማስወጫው በአዲሱ አቅጣጫ ሲቀየር የውሃ ማስቀየሻው ግድብም 210 ሜትር ወደ ታች እንዲወርድ ተደርጓል፡፡

አዲሱ የኮርቻ ግድብ ሥራ ዲዛይን እና ቦታ ቅየራ እየተሰራ ባለበት የማጠናቀቂያ ጊዜው ሰኔ 30/2012 ዓ.ም ደረሰ፡፡ ይህንም አማካሪው ቀጣይ ጥናት (ምርመራ) ከአደረገ በኋላ የኮርቻ ግድብ ሥራ ገና ሥለሆነ የጊዜ ማራዘሚያ አዘጋጅቶ ባለቤቱ እንዲያፀድቅ አቀረበ፡፡ በዚህ ምክንያት አማካሪው ከሐምሌ 1/2012 እስከ ሰኔ 30/2013 ዓ.ም የሚሆን የጊዜ ማራዘሚያ አዘጋጅቶ ባለቤቱ እንዲያፀድቅለት አቀረበ፡፡ በዚህ ጊዜ አዲሱ የኮርቻ ግድብ ከመነሻው ከኮርቻ ግድብ 1ና2 የምህንድስና (ኢንጂነሪንግ) ግምት እና ከውል ዋጋ በላይ ሆነ፡፡ ዋናው ተቋራጭ ደግሞ ይህን ሥራ የሚሰራለት ንዑስ ኮንትራክተር በግልፅ ጨረታ ቀጠረ፡፡ አሸናፊ የሆነው ንዑስ ኮንትራክተር ዝቅተኛ ያቀረበውና ያሸነፈበት ዋጋ የዋጋ ማሻሻያ ከተደረገበት ቁጥር 03 የፕሮጀክት ዋጋ በአማካይ 19.3 በመቶ በላይ ሆኖ መጣ ፡፡

በሌላ በኩል ግሩቲንግ ሥራዎች (grouting works) ነጠላ ወጋ በውል ማሻሻያ ቁጥር 03 የተካተተ ባለመሆኑ ዋጋ አልተሰጠውም ነበር፡፡ በዚህ ምክንያት ተቋራጩ (የኦሮሚያ ኮንስትራክሽን ኮርፖሬሽን) የቀሩት የግሩቲንግ ሥራዎች የነጠላ ዋጋ ማሻሻያ እንዲደረግለት አመለከተ፡፡ በዚህም ኮንትራክተሩ ለነጠላ ዋጋ ማሻሻያ (የግሩቲንግ ሥራዎች) በቀን የካቲት 18/2013 ዓ.ም አቀረበ፡፡ ከዚያም ዋናው ተቋራጭ የንዑስ ኮንትራክተር ያቀረበው የነጣላ ዋጋ በዝቅተኛው የጨረታ ዋጋ የፕሮጀክቱን (የግሉቲንግ ሥራዎችን) ዋጋ 25 በመቶ እንደሆነ አቅርቧል፡፡ በዚህ መሰረት የአዲሱ ኮርቻ ግድብ ግሩቲንግ ሥራዎች የነጠላ ዋጋ ማሻሻያ ቁጥር 04 አርጆ ዲዴሳ ግድብ ግንባታ ሎት-1 ሆነ፡፡ ይህም የግሩቲንግ ሥራ የነጠላ ዋጋ ማሻሻያ ቁጥር 04 እና ቀሪ ዝርዝር ሥራዎች የኮርቻ ግድብ ግሩቲንግ ሥራ ተብሎ ተሸሻለ፡፡

በአዲሱ የኮርቻ ግድብ ምክንያት የሥራ መጠንና የዋጋ ልዩነት በመምጣቱ እንደገና ዲዛይን እንዲሻሻል በመደረጉ የውል ስምምነት ቁጥር 04 ተሻሻለ፡፡ ኮርቻ ግድብ አንድ(1) እና ሌሎች የተወሰኑ ሥራዎች ከዋና ግድቡ ውስጥ እንዲቀነሱ ተደርጓል፡፡ አዲሱ የኮርቻ ግድብ ዓላማ የነበረውን የኮርቻ ግድብ 1እና2 እንዲተካ ተደርጎ ነው የተዘጋጀው፡፡ በመሆኑም ከኮርቻ ግድብ 2 ያልተሰሩ ቀሪ ሥራዎች ከውል ማሻሻያ ቁጥር 03 እንዲቀነሱ (Ommited) ተደርጓል፡፡

**የውል ማሻሻያ ቁጥር 05**

የውሃ ማስተንፈሻው እና የቀኝ እና የግራ ውሃ ማስወጫ ግንባታዎች ከመጀመሪያው የአርጆ ዲዴሳ ግድብ ግንባታዎች ፕሮጀክት ውስጥ እንዲወጡ ተደርጓል፡፡ በዚህ ምክንያት የዲዛይን ክለሳ እንዲደረግ ሆኗል፡፡ በመሆኑም ባለቤቱ እና ተቋራጩ ተስማምተው የውል ማሻሻያ ቁጥር 05ን በቀን ጥር 09/2015 ዓ.ም ተፈራረሙ፡፡ በዚህ ጊዜ የፕሮጀክቱ አፈጻጸም ደረጃ 94.5 በመቶ ሲሆን የፋይናንስ አፈጻጸም ደግሞ 83 በመቶ ነበር፡፡ ለፕሮጀክቱ የውል ማሻሻያ ቁጥር 05 የውል ማጠናቀቂያ ጊዜ የተሰጠው እስከ ግንቦት 15/2016 ዓ.ም ነው፡፡

**የውል ማሻሻያ ቁጥር 06**

በአጠቃላይ የአርጆ ዲዴሳ የፕሮጀክት አፈፃፀም የዘገየባቸው ዋና ዋና ምክንያቶች፡- በፕሮጀክቱ ግንባታ አካባቢ ረጅም ጊዜ የዝናብ ወቅት መኖሩ፣ የውሃ ማስተንፈሻ የመሰረት ሥራ መዘግየት (Spill way construction or Pile works)፣ ሲሚንቶ በገበያ ላይ እጥረት መፈጠሩ፣ የፀጥታ ችግር በአካባው መኖር ናቸው፡፡ ተቋራጩ የፕሮጀክቱ ማጠናቀቂያ ጊዜው በ365 ቀናት እንዲራዘምለት ከግንቦት 24/2016 እስከ ግንቦት 23/2017 ዓ.ም. ጠይቋል፡፡ ይህ ጥያቄ በአማካሪው ተቀባይነት አግኝቶ 365 ቀናቱ እንዲፈቀድለት ለባለቤቱ እንዲፀድቅ አቅርቧል፡፡

የውል ማሻሻያ ቁጥር 06 የተደረገበት ምክንያት፡- ቀሪውን 17 በመቶ የፋይናን አፈጻጸም ለማጠናቀቅ፣ የተከናወኑ የፕሮጀክቱ ሥራዎች መጠን መረጋገጥ በማስፈለጉ፣ የሚጨመሩና የሚቀነሱ ዝርዝር ሥራዎች በመኖራቸው፡፡ የዉል ማሻሻያው ቁጥር 06 አስፈላጊ በመሆኑ ነው፡፡

## 3.9.3. የወይቦ ግድብ እና ተያያዥ ስራዎች የመስኖ ልማት ፕሮጀክት ግልጽነት፣

### 3.9.3.1. የወይቦ ፕሮጀክት ያለበት ደረጃ፣

ፕሮጀክቱ በደቡብ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግስት ወላይታ ሶድ ዞን፣ ቦልንሳ ሶሬ እና ቦልንሳ ቦንቤ ወረዳ የሚገኝ ሲሆን ሲጠናቀቅም 3,371 ሄክታር መሬት በዘመናዊ መስኖ የማልማት አቅም ይኖረዋል፡፡ የሎት-1 ፕሮጀክቱ የግድብ እና ተጓዳኝ ስራዎች ግንባታን 2016 በጀት ዓመት መጨረሻ 13.3% የደረሰ ሲሆን፣ የመሠረተ ልማት ግንባታው (ሎት 2) ስራ 2016 በጀት ዓመት መጨረሻ 16.11% መሆኑን መረጃዎች ያሣያሉ፡፡ በ2017 በጀት ዓመት የመጀመሪያው ሩብ ዓመት የፕሮጀክቱን የሎት-1 ስራ 0.15% ለማከናወን ታቅዶ ምንም ሳይከናወን ቀርቷል፡፡ የፕሮጀክቱን ሎት-2 ስራ በሩብ ዓመቱ 0.15% ለማከናወን ታቅድ 0.86% ወይም የዕቅደን ከ100% በላይ ተግባራዊ በማድረግ አጠቃላይ  የሎት-2ን የግንባታ አፈጻጸም 16.97% ማድረስ ተችሎል፡፡ የዚህ ፕሮጀክት ዋናው ችግር የወሰን ማስከበር ችግር ሲሆን ሎት-1 ላይ ስራውን ሲሰራ የነበረው ስራ ተቋራጭ ደቡብ ውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ነበር፡፡ ነገር ግን  ክልሉ ወደ ተለያዩ ክልሎች በመፍረሱ ምክንያት ስራው ሊቋረጥ ችሏል፡፡ በዚህ በጀት አመት ወደ ስራ ለማስገባት ቢታሰብም የወሰን ማስከበር ችግሩ ሙሉ ለሙለ በክልል መፈታት ስለሚኖርበት ክልል ሃላፊነት እንዲወስድ ተጠይቋል፡፡ በሌላ በኩል ከዚህ በፊት ዲዛይኑን ለሰራው አማካሪ ድርጅት ሊያስነሳው የሚችለውን የማህበረሰብ ክፍል ጫና በሚቀንስ መልኩ የዲዛይን ክለሳ ሰርቶ እንዲያመጣ ታዟል፡፡ የ2017 የፋይናንስ አጠቃቀምን በተመለከተ ለመጀመሪያው ሩብ ዓመት ለፕሮጀክት ሎት-2 ማስፈጸሚያ 4.14 ሚሉዮን ብር ታቅዶ 4.04 ሚሊዮን ወይም የዕቅዱን 97.58 በመቶ ወጪ ሆኖ ሥራ ላይ ውሏል፡፡

### 3.9.3.2. የወይቦ ግድብ እና ተያያዥ ስራዎች የመስኖ ልማት ፕሮጀክት ግዥ አፈጻጸም ግልጽነት፣

የወይቦ የመስኖ ልማት ፕሮጀክት የአዋጭነት እና የአካባቢ ተፅዕኖ ጥናት የተካሄደ ሲሆን፣ አማካሪዎች የተወዳደሩበት የዲዛይንም ሆነ የሱፐርቪዥን ግዥ አፈጻጸም ሰነዶች  በሚ/ር መ/ቤቱ አልተገኘም፡፡ የሥራ ተቋራጩ ጨረታ የወጣበት ቀን ጥቅምት 20/2013 ዓ.ም

ነው፡፡ ለሎት2 ተቋራጭነት ግዥ ጨረታ የተካሄደበት የግዥ ዘዴ በግልፅ ጨረታ ነው፡፡ የጨረታ ሰነድ የገዙት 7ቱም ተጫራቾች ለውድድር ቀርበዋል፡፡ ሎት-1 ጨረታ ግን በቀጥታ ግዥ ዘዴ የተፈፀመ ነው፡፡ ፕሮጀክቱን ለመገንባት  የተመረጡት ለሎት-1 ደቡብ ውሃ ሥራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት ሲሆን፣ ለሎት-2 አሸናፊ የሆኑት ክሮስ ላንድ ጂቪ ከኦሮሚያ ኮንስትራክሽን ኮርፖሬሽን ጋር ነው፡፡ ለሎት-1 እና 2  ለዲዛይን ሥራው እና ለሱፐርቪዥን ጨረታውን አሸናፊ ሆኖ የተቀጠረው ደቡብ ዲዛይንና ኮንስትራክሽን ቁጥጥር ድርጅት ነው፡፡ የወይቦ ሎት-2 የመስኖ ልማት እና ዲሬኔጅ ሲስተም ኮንስትራክሽን ግንቦት 06/2013 ዓ.ም በመስኖ ልማት ኮሚሽን እና ክሮስ ላንድ ኮንስትራክሽን ጂ.ቪ(J.V) ከኦሮሚያ ኮንስትራክሽን ጋር በመሆን የሥራ ውል ተዋውለዋል፡፡ የወይቦ ፕሮጀክት ሎት-2 የጨረታ ውል የተፈረመው ታህሳስ 08/2013 ዓ.ም ነው፡፡

## 3.9.3.3. የፕሮጀክቱ የውል ጊዜ እና ዋጋ ስምምነቶች ግልጽነት፣

የወይቦ መስኖ ልማት ፕሮጅክት የሎት-1 የኮንትራክት ውል በመስኖ ልማት ኮሚሽን እና በደቡብ ውሃ ሥራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት መካከል የተፈረመው ስምምነት ግንቦት 30 /2013 ዓ.ም  ነው፡፡ ለሎት-1 ግንባታ ሥራዎች የሚውል መነሻ በጀት የተመደበው 1,404,113,759.02 ብር ነው፡፡  ለሥራው ማጠናቀቂያ ጊዜ የተሰጠው 24 ወራት ነው፡፡ የዋጋ ማሻሻያ እንደሚደረግለት በአጠቃላይ የኮንትራክት ውል ሁኔታ (ጂ.ሲ.ሲ) 62.7እና62.13 ላይ ተቀምጧል፡፡ የሎት-1 ፕሮጀክት ተቋራጩ በውል ስምምነቱ መሰረት የተደረገው ቅድሚያ ክፍያ የግንባታ ውል መነሻ ዋጋውን 20 በመቶ ብቻ ነው፡፡

የወይቦ መስኖ ልማት ሎት-2 ፕሮጀክት መነሻ ዋጋ **1,031,374,587.03** ብር ነው፡፡ ለሥራ ማጠናቀቂያ ጊዜ የተሰጠው 18 ወራት ነው፡፡ ተቋራጩ ተጨማሪ የሥራ ትዕዛዞች በመሰጠታቸው ምክንያት ሎት-2 ፕሮጀክት የውል ማሻሻያ መነሻ ዋጋ 1,248,412,635.12 ብር እንዲሆን ተደርጓል፡፡ የተደረገው የዋጋ ማሻሻያ ልዩነት ብር 217,038,050.09 ነው፡፡

የውል ማሻሻያ ቁጥር 01 በሚ/ር መ/ቤቱ እና በአማካሪ ድርጅቱ (ደቡብ ዲዛይን እና ኮንስትራክሽንና ሱፐርቪዥን ድርጅት) መካከል መስከረም 27/2014 ዓ.ም ለ24 ወራት የሚቆይ ስምምነት በ 32,384,920.00 ብር ተዋውለዋል፡፡


የሎት-2 የዋጋ ማስተካከያ በውል መሰረት አይመለከተውም (price adjustment is not allowed) ይላል፡፡ ነገር ግን በሚ/ር መ/ቤቱ እና በኮንትራክተሩ መካከል ቁጥር አንድ(1) የዋጋ ማስተካከያ መስከረም 29/2016 ዓ.ም ተደርጓል፡፡ ምክንያቱም የዋጋ ማስተካከያ የተደረገው ከመንግስት ግዥ ኤጀንሲ በተፃፈላቸው ደብዳቤ መሰረት በአዋጅ ቁጥር 649/2001 አንቀጽ 54 መሰረት የገንዘብ ሚ/ር የዋጋ ማስተካከያ ፋክተር ወጥ እንዲሆን  እንዲደረግ በቀን 25/06/2013 ዓ.ም በሰርኩላር የተገለፀ መሆኑን መረጃው ያሳያል፡፡ በመሆኑ  ለዋጋ ማስተካከያ የተደረገው የገንዘብ መጠን 16,825,729.15 ብር ነው፡፡

## 3.9.3.4. የወይቦ ፕሮጀክት ካሳ ክፍያ አፈጻጸም ግልጽነት፣

የወይቦ ፕሮጀክት ለተነሽዎች የካሳ ክፍያ የተጠየቀበት ደብዳቤ አልተገኘም፡፡ ነገር ግን ከህዳር 21/2021- ህዳር 20/2024 እ.ኤ.አ. በInvoice No 00012231 ብር 70,654,257.00፣ በInvoice No 00022163 ብር 63,966,639.39  በጠቅላላው 134,520,896.39 ብር  ለተነሽዎች 134,520,896.36 ብር ቅድሚያ የካሳ ክፍያ ተከፍሏል፡፡ ከዚህ ውስጥ 11,934,1191.5 ብር የያዘ ሂሳብ የዚህ ጥናት መረጃ እስከተሰበሰበበት ድረስ አልተወራረደም፡፡ በዚህ ምክንያት ቅድሚያ የተከፈለው ካሳ ክፍያ ለተጠቃሚዎች በአግባቡ የደረሰ መሆኑን እና አለመሆኑን ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

## 3.4. የፕሮጀክቶች መዘግየት ምክንያት የሆኑ አካላትን የሚያሳይ ሰንጠረዥ 09

| ተ.ቁ | **የፕሮጀክቱ መዘግየት ምክንያቶች** | **የፕሮጀክቱ ባለቤት** | **ተቋራጩ** | **አማካሪው** | **ሌሎች ውጫዊ ሁኔታዎች** |
|---|---|---|---|---|---|
| 1. | የዲዛይን ችግር | | | ✓ | |
| 2. | የካሳ ክፍያ ችግር | ✓ | | | |
| 3. | አዳዲስ ተጨማሪ ሥራዎች መስጠት | ✓ | | | |
| 4. | ሥራዎችን መጨመር (መቀነስ) | ✓ | | | |
| 5. | የወሰን መቀየር | ✓ | | | |
| 6 | የፋይናንስ ችግር | ✓ | | | |
| 7. | የጥራት ጉድለት | | ✓ | | |
| 8 | የጊዜና የዋጋ ግምት ስህተት | | | ✓ | |
| 9 | የልምድ እጥረት | | ✓ | | |
| 10 | የክትትልና ቁጥጥር ማነስ | | | ✓ | |
| 11. | የፀትታ ችግር | | | | ✓ |
| 12. | የእቃዎጭ አቅርቦት እጥረት | | | | ✓ |
| | **ድምር** | **5** | **2** | **3** | **2** |
| | **በመቶኛ** | **42%** | **16.5%** | **25%** | **16.5%** |
| | | | | | |




ከላይ በግራፉ እንደሚታየው ለፕሮጀክቶች መዘግየት በአንደኛ ደረጃ የፕሮጀክቱ ባለቤት በ42 በመቶ ድርሻ ያለውና ኃላፊነት የሚወስድ ሲሆን፣ በሁለተኛ ደረጃ በ25 በመቶ አማካሪው፣ በ3ኛ ደረጃ ተቋራጩ እና ውጫዊ ጉዳዮች መሆኑን ጥናቱ ያሣያሉ፡፡

## 3.5. የልማት ተነሽዎች የካሳ ክፍያ ግልጽነትን በተመለከተ፣

የልማት ተነሽ ካሳ፡- ባለይዞታው የመሬት ይዞታውን ሲለቅ በመሬቱ ላይ የመጠቀም መብቱ በመቋረጡ ምክንያት የሚደርስን ጉዳት ለማካካስ የሚከፈል ክፍያ ነው፡፡ ካሳ የሚከፈልበት ሁኔታ የመሬት ይዞታ እንዲለቀቅ የተወሰነ በፌደራል መንግስት ለሚከናወን መሰረተ ልማት እና ማህበራዊ አገልግሎት ማስፋፊያ ከሆነ የልማት ሥራው የሚካሄድበት ክልል አስተዳደር ለባለይዞታዎች የሚከፈለውን የንብረት ካሳ፣ የልማት ተነሽ ድጋፍ፣ የኢኮኖሚ ጉዳት ካሳ፣ የማህበራዊ ትስስር መቋረጥ፣ የሥነ ልቦና ጉዳት ካሳ ወጪ የመክፈል ግዴታ አለበት (የመሬት ይዞታ የሚለቀቅበት፣ካሳ የሚከፈልበት እና ተነሽዎች መልሰው የሚቋቋሙበትን ሁኔታ ለመወሰን የወጣ አዋጅ ቁጥር 1161/2011) መሰረት የመስኖ እና ቆላማ አካባቢ ሚ/ር ለመስኖ ግድብ እና ልማት ተነሽዎች የካሳ ክፍያ በተለያዩ ጊዜ እንደሚከፍል መረጃዎች ያሳያሉ፡፡

**ሰንጠረዥ 10 የካሳ ክፍያ የተፈፀመላቸው መሆኑን የሚያሳይ ሠንጠረዥ**

| ተ.ቁ | የፕሮጀክቱ ሥም | የተከፈለበት ቀን እ.ኤ.አ | ቅድሚያ ክፍያ የተከፈለው ገንዘብ በብር | የተወራረደው ገንዘብ በብር | ያልተወራረደ ገንዘብ በብር |
|---|---|---|---|---|---|
| 1. | ርብ ግድብ ፕሮጀክት (ፎገራ ወረዳ) | From Nov20/2020—Nov 20/2024 | 230,039,387.41 | 34,357,649.00 | 195,681,738.33 |
| 2 | ወይቦ መስኖ ልማት ፕሮጀክት(በሎሴ ሶሬወረዳ) | From Nov20/2020— Nov 20/2024 | 134,520,896.39 | 119,341,191.50 | 15,179,704.89 |
| 3 | ካሊድ ዲጆ ፕሮጀክት | From Nov20/2020— | 72,123,049.00 | 72,123,049.00 | 00.00 |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | (ዳሎቻ ወረዳ) | Nov 20/2024 | | | |
| | | | | | |

**ምንጭ**:ከመስኖ እና ቆላማ አካባቢ ሚ/ር.

ከላይ በሠንጠረዡ እንደሚታየው ለካሳ ክፍያ ተብሎ በሚ/ር መ/ቤቱ የተከፈለው የቅድሚያ ክፍያ የካሳ ገንዘብ ለባለይዞታዎች በአግባቡ የደረሰ መሆኑን ለማወቅ በተደረገው ጥናት በርብ እና በወይቦ ፕሮጀክቶች ብር 210,861,443.22 ያልተወራረዱ እና ለሚመለከታቸው አካላት የደረሰ ስለመሆኑ የሚያሳይ ማስረጃ የለም፡፡ ይህም በተቋሙ የተከፈለው የካሳ ቅድሚያ ክፍያ ገንዘብ በትክክል ለባለይዞታወቹ የደረሰ ለመሆኑ ለሚ/ር መ/ቤቱ በመረጃ የተደገፈ ሪፖርትም ሆነ ማስረጃ ያልደረሰው መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

**ሰንጠረዥ ቁ.10 ለመስኖ ልማት ፕሮጀክቶች ካሳ ክፍያ ተጠይቆ ያልተከፈለ ገንዘብ ዝርዝር፣**

| ተ.ቁ | የመስኖ ፕሮጀክት ስም ዝርዝር | ለልማት የተወሰደ መሬት ስፋት በሄ/ር | የልማት ተነሽዎች ብዛት | የተጠየቀው ገንዘብ መጠን |
|---|---|---|---|---|
| 1 | የላይኛው ርብ መስኖ ልማት ፕ/ት | 61.1987 | 348 | 354,736,570.00 |
| 2 | አጇማ ጫጫ መስኖ ልማትፕሮጀክት | 74.83 | 454 | 193,018,158.41 |
| 3 | ወይቦ መስኖ ል/ፕሮጀክት | 26.96 | 323 | 168,246,196.00 |
| 4. | መገጭ ግድብ ፕሮጀክት | 10.7347 | 18 | 32,447,367.58 |
| 5 | ወልመል መስኖ ል/ፕሮጀክት | 144.16 | 389 | 54,956,768.70 |
| 6 | የላይኛው ጉደር መስኖ ል/ትፕሮጀክት | 5.9925 | 15 | 20,920,848.60 |
| | **ድምር** | **323.8759** | **1,594** | **824,325,909.38** |

ምንጭ:-መስኖና ቆላማ አካባቢ ሚ/ር የፋይናንስ የሥራ ሂደት

ከላይ በሰንጠረዡ እንደሚታየው 6 ፕሮጀክቶች 1,594 የልማት ተነሺ ሰዎች ከ2015 ዓ.ም ጀምሮ ብር **824,325,909.38** ካሳ እንዲከፈላቸው የተጠየቁ ቢሆንም እስካሁን ድርስ ያልተከፈላቸው መሆኑን መረጃዎች ያሳያሉ፡፡

በመስክ ጉብኝት እንደተረጋገጠው በአጅማ ጫጫ መስኖ ልማት ፕሮጀክት የልማት ተነሽዎች መሬት ተለክቶ ወደ ሚ/ር መ/ቤቱ የተላለፈው ከ500 ሚሊዮን ብር በላይ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ከዚህ ገንዘብ ውስጥ ለባለይዞታዎች ሳይከፈል ለወደፊት ይከፈላችኋል ተብሎ ለግንባታ የዋለው ጥሬ ዕቃ እና ለካናል ሥራ የተሰራው 24 ኪሎ ሜትር የመዳረሻ መንገድ ግንባታ ሥራ የተሰራው እንኳ ከላይ በሰንጠረዡ እንደሚታየው ብር 193,018,158.41 እዳልተከፈላቸው ለማወቅ ተችሏል፡፡ ይህ ያልተከፈለው የካሳ ክፍያ ከ4 ዓመት በላይ ሆኖታል፡፡ የአጅማ ጫጫ ግድብ የግንባታ ሥራ እናተያያዥ ሥራ ፕሮጀክት በ4 ዓመት ውስጥ አፈጻጸሙ 64 በመቶ የደረሰ መሆኑ የሚ/ር መ/ቤቱ የእቅድ አፈጻጸም ሪፖርት ያመላክታል፡፡

ከወረዳው አስተዳዳሪዎች ጋር በተደረገ ውይይት አጅማ ጫጫ ፕሮጀክት ከ2015 ዓ.ም ጀምሮ አስካሁን ድረስ 584 ሰዎች በወረዳው ልኬት ተለክቶ ካሳ እንዲከፈላቸው ከ700 ሚሊዮን ብር በላይ ለሚ/ር መ/ቤቱ የተላከ ቢሆንም እስከ አሁን ድረስ የተከፈለው 100 ሚሊዮን ብቻ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡ በተለይ 64 በመቶ የፕሮጀክት ሥራው ሲሰራ ጥቅም ላይ ለዋለ ጥሬ እቃ እና የሎት አንድ እና ሁለት ካናሎች 24 ኪሎ ሜትር የካናል ሥራ እና የመዳረሻ መንገድ ግንባታ የተገነባው ለባለይዞታዎች ካሳ ሳይከፈል ወደ ፊት ይከፈላችኋል ተብሎ ነበር፡፡ ፕሮጀክቱ

አስቀድሞ የተጠቀመበትን የጥሬ እቃና የግንባታ መሬት ካሳ ብር 193 ሚሊዮን በላይ ለባለይዞታዎች አልተከፈላቸውም፡፡ ግድቡ የተገነባበት መሬት እና ለግንባታ የተጠቀመበት ግብዓት ተብሎ መሬቱ የተወሰደባቸው ሰዎች ካሳ ባለመከፈሉ ምክንያት ከዚህ በኋላ ላለው ግንባታ እንቅፋ እየሆነባቸው መሆኑን አመላክተዋል፡፡ ባለይዞታዎች በይዞታቸው ውስጥ የሚገኘውን ጥሬ እቃ ተቋራጩ እንዳይጠቀም መከልከላቸውን በፕሮጀክት ሳይት ላይ ካሉ ባለሙያዎች ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

እንዲሁም በሚ/ር መ/ቤቱ እና በኮንትራክተሩ መካከል የዕቅድ ክንውን አፈጻጸም ሪፖርት ላይ የሚታይ አለመግባባት መኖሩን ያሳያል፡፡ ይህ ደግሞ የፕሮክቶችን አፈጻጸም ሊያጓትት ይችላል፡፡ ለምሳሌ የአጅማ ጫጫ ፕሮጀክት የሥራ አፈጻጸም ዝቅተኛ ነው ለማለት የሚደረጉ የአፈጻጸም ሪፖርቶች አቀራርብ ችግር ያለበት መሆኑን ገልፀዋል፡፡ ፕሮጀክቱ ከሌሎች የፕሮጀክቶች አፈጻጸም አንፃር የተሸለ አፈጻጸም ቢኖረውም በሪፖርት ግምገማ ወቅት የሚገመገመው በአመቱ ከተያዘው ዕቅድ አንጻር ሳይሆን በተለያዩ ምክንያት ከአቅም በላይ በሆኑ ጉዳዮች ከዘገየው ከአጠቃላይ ፕሮጀክቱ አፈጻጸም አንጻር በመሆኑ የዓመቱ አፈጻጸም ሪፖርት ዝቅተኛ እንዲሆን እየተደረገ መሆኑን ገልፀዋል፡፡ ይህ ደግሞ አለመግባባት እና ጭቅጭቅ እየፈጠረ በመሆኑ የሪፖርቱ ችግር ታይቶ ማስተካከያ እንዲደረግላቸው ጠይቀዋል፡፡

በመሆኑም በአጠቃላይ ሚ/ር መ/ቤቱ ለአጅማ ጫጫ ፕሮጀክት ከዚህ በፊት ጥቅም ላይ የዋሉ የጥሬ እቃ እና ካናል ግንባታ ሥራዎች እና ለወደፊት የሚጠቀሙባቸውን ጥሬ ዕቃዎች ካሳ በመክፈል እና የዕቅድ ክንውን አፈጻጸም ግምገማን የዓመቱን ዕቅድ በዓመት በመገምገም በጥሩ ሀኔታ ላይ ያለው ፕሮጀክት በአለበት እንዲቀጥል ለማደረግ ጥረት ካልተደረገ ፕሮጀክቱ እንደሌሎች የፕሮጀክት ግንባታዎች ሥራ አላግባብ እንዲጓተት በማድረግ በእቃዎች ዋጋ መጨመርና በዋጋ ማሻሻያ ምክንያት መንግስት ከካሳ ክፍያው በላይ ተጨማሪ ወጪ እንዲያወጣ በማድረግ አሰራሩ ለሀብት ብክነት እንዲጋለጥ ሊያደርገው ይችላል፡፡

## 3.6. ተሰብሳቢ ሂሳብ እና ተከፋይ ሂሳቦችን በሚመለት፤

በመስኖና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር የመስኖ ልማት ፕሮጀክቶች ጋር በተያያዘ ተሰብሳቢ ሂሳቦቹ ሳይወራረዱ የሚታዩ ሂሳቦች፣ የሂሳብ መግለጫዎቹን ተዓማኒነት ሊያሳጡ ከመቻላቸውም በላይ የመንግሥት ገንዘብ ለብክነትና ለጥፋት ሊዳረግ የሚችል ስለሆነ ሚ/ር መሥሪያ ቤቱ በመንግሥት የፋይናንስ ደንብና መመሪያ መሰረት ክፍያ ሂሳቦች እንዲወራረዱ፤ መሰብሰብ የማይችሉትን ደግሞ አጣርተው አስፈላጊውን እርምጃ መወሰድ አለበት፡፡ እንደሚሰበሰብ የማይታወቀው ደግሞ ተጣርቶ በማስረጃ እንዲረጋገጥና መሰብሰብ ያለባቸው መሰብሰብ ኢንዲችሉ ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡ የጥናት ቡድኑ የመስኖ ልማት ፕሮጀክቶች መረጃዎችን በሰበሰበበት ጊዜ ተሰብሳቢ ሂሳብ ሰኔ 2016 ዓ.ም ሪፖርት ላይ በጠቅላላው ብር 15,388,404,013.86 መኖሩን ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ በዝርዝር ሲታይ ከካሳ ክፍያ ብር 903,324,306.99፣ ከግንባታ እና ሱፐርቪዥን ብር 14,349,534,020.05፣ ከግዥ ብር 122,349,865.88፣ ከግለሰቦች ብር 1,114,792.36፣ ሌሎች በሚል ብር 11,991,028.58 ተሰብሳቢ መኖሩን መረጃዎች ያሣያሉ፡፡

እንዲሁም የተከፋይ ሂሣብን በሚመለከት በመስኖ እና ቆላማ አካባቢ ሚ/ር መ/ቤት ብር 2,472,542,685.09 በወቅቱ ያልተከፈለ የፕሮጀክት የተከፋይ ሂሳብ መኖሩን መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ በዚህ የተመለከተው ውዝፍ ተከፋይ ሂሳብ ተጣርቶ በፋይናንስ ህጉ መሰረት ለሚመለከታቸው አካላት እንዲከፈል ቢደረግ የተሻለ ነው፡፡ በተከፋይ ሂሳብ የተመዘገበና ዝርዝር ማስረጃ ባለመቅረቡ የሂሳቡን ትክክለኛነት ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

## 3.7. በመስኖ እና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር የመስኖ ልማት ፕሮጀክቶች ውጤታማነት፣

የመስኖ ፕሮጀክቶቹ ወደ ልማት ከገቡ በኋላ የመስኖ ልማት አፈፃፀማቸውን ለመከታተል የሚያስችሉ ስታንዳርዶችና መመሪያዎች የሌሉ መሆኑ፤ እንዲሁም የመስኖ ውሃ ተጠቃሚዎች ደንብና መመሪያ ያልተዘጋጀ መሆኑ እና የውሃ አጠቃቀም ስትራቴጂ የሌለ መሆኑ መረጃወች ያሳያለ፡፡ በዚህና በሌሎች ተጨማሪ ችግሮች ምክንያት የመስኖ ልማት ፕሮጀክቶች ውጤታማ አይደሉም፡፡

**የመስኖ ልማት ፕሮጀክቶች ከተጠናቀቁ በኋላ እየለማ ያለውን መሬት በሄክታር የሚያሳይ ሠንጠረዥ10.**

| ተ.ቁ | የፕረጀክቱ ሥም | የማልማት አቅሙ በሄክታር | እየለማ ያለው መሬት በሄክታር | የለማው መሬት በመቶኛ | ምርመራ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1. | ተንዳሆ የመስኖ ልማት ፕሮጀክት | 60,000 ሄክታር | 25,000 ሄክታር | 41.6% | አገልግሎት አይሰጥም |
| 2. | ከሰም የመስኖ ልማት ፕሮጀክት | 20,000 ሄክታር | 2,784 ሄክታር | 14% | |
| 3. | የመካከለኛው አዋሽ የመስኖ ልማት ፕሮጀክት፡- | 120,000 ሄክታር | 20,000 ሄክታር | 16.6% | |
| 3. | የታችኛው አዋሽ የመስኖ ፕሮጀክቶች | 25,152 ሄክታር | 4,000 ሄክታር | 15.9% | |
| 5. | ጎዴ የመስኖ ልማት ፕሮጀክት | 27,600 ሄክታር | 2,000 ሄክታር | 7.3% | |
| 6. | ኦሞ ኩራዝ የመስኖ ፕሮጀክት | 175,000 ሄክታር | 25,000 ሄክታር | 14% | |
| 7. | ጣና በለስ የመስኖ ፕሮጀክት | 50,000 ሄክታር | 15,000 ሄክታር | 30% | |
| 8. | ርብ የመስኖ ልማት ፕሮጀክት | 4000 ሄክታር | 0 ሄክታር | 0 | |
| | **አማካይ** | | | **17.4%** | |

ከላይ በሰንጠረዡ እንደሚታየው በናሙና ከታዩ 8 ፕሮጀክቶች ከተጠናቀቁ በኋላ እያለሙት ያለው መሬት በመቶኛ ሲታይ ከፍተኛው ተንዳሆ የመስኖ ልማት ፕሮጀክት 41.6%፣ ዝቅተኛው ጎዴ የመስኖ ልማት ፕሮጀክት 7.3% እያለማ ሲሆን፣ በአማካይ እየለማ ያለው መሬት 17.4% ብቻ መሆኑ፣ የናሙናው 75% የለማው መሬት ከአማካይ በታች መሆኑ በበዘርፉ የተጠናቀቁ የመስኖ ልማት ፕሮጀክቶች ውጤታማነት ዝቅተኛ መሆኑን ያሳያል፡፡

## ምዕራፍ አራት

## የጥናቱ ዋና ዋና ግኝቶች

1. በናሙና ከታዩት 8 የመስኖ ልማት ፕሮጀክቶች አማካሪዎች 100% እና ተቋራጮች 87% በደብዳቤ በመጋበዝ ያለውድድር በቀጥታ ግዥ ዘዴ የተፈጸሙ መሆኑ፣
2. የመስኖ ፕሮጀክቶች ለዲዛይን ዝግጅት እና ለሱፐርቪዥን ሥራዎች አንድ አማካሪ በመቅጠር አማካሪው ራሱ የሰራውን ዲዛይን ራሱ የሚያስተካክልበት እድል በመፍጠር ሚዛናዊ ቁጥጥርን በማላላት ግልጽነትን እና ተጠያቂነትን በመቀነስ ለጥቅም ግጭት የሚያጋልጥ መሆኑ፣
3. ለአንድ ድርጅት (ተቋራጭ) በተመሳሳይ ጊዜ በርካታ የፕሮጀክት ሥራዎችን በመስጠት ወይም እንዲሰሩ በማድረግ የሥራ ክብደትን፣ የጊዜ መጣበብን፣ የማሽነሪዎችና የሰው ሃይል እጥረት በመፍጠር ግንባታው በወቅቱና በታቀደለት ጊዜ እንዲጠናቀቅ አለማድረግ እና በግንባታው ጥራት

ላይ በመደራደር (Compromised) ወይም በስምምነት ለግል ጥቅም እንዲውል በማድረግ መንግስት አላግባብ ተጨማሪ ወጪ እንዲያወጣ እና የግንባታው ጥራት እንዲጓደል ማድረጉ፣

4. የተቋራጮች ግዥ ሲፈፀም የምህንድስና ግምት ሳይሰራ በድርድር ዋጋ መስጠት፣ (መገጭ ግድብና አርጆ ዲዴሳ ግድብ እና ሌሎችም)፣
5. በአንድ ጨረታ ተጠቃሎ የተፈፀመ የፕሮጀክት ግዥን እንደገና በሎት ከፋፍሎ (spilit) ከመጀመሪያው ግንባታ ውስጥ እንዲወጡ አድርጎ በመስጠት በአዲስ መልክ የዋጋ ማስተካከያ እና የውል ዓይነት ለውጦች ማድረግ፣ ከፋፍሎ ውል መዋዋል (spilit)፣ አዲስ የነጠላ ዋጋ መትከል እና አዲስ የውል ማሻሻያ በማድረግ መንግስት ከፍተኛ ተጨማሪ ወጪ እንዲያወጣ ማድረጉ፣
6. የግዥ ሰነዶች መረጃ አያያዝ ደካማ መሆን፣( በግንባታ ላይ የሚገኙ ፕሮጀክቶች የአብዛኞች የግዥ ሰነዶች አለመኖር፣)
7. የአዋጭነት ጥናት በአግባቡ አለማጥናት እና አዋጭነት በሌላቸው ወይም አነስተኛ የኢኮኖሚ አዋጭነት ባላቸው የመስኖ ልማት ፕሮጀክቶች ላይ ከፍተኛ በጀት መመደብ፣ ( ቋጦ እና ካሊድ ዲጆ ፕሮጀክቶች)
8. በናሙና የታዩት የመስኖ ፕሮጀክቶች በተቀመጠላቸው የማጠናቀቂያ ጊዜ ባለማጠናቀቅ ምክንያት ተጨማሪ ጊዜ በአማካይ 98 ወራት (354.6%) እና ተጨማሪ በጀት በአማካይ ብር 6,168,408,663.96 ወይም 422.4% የደረሰ መሆኑ፣ እንዲሁም የእነዚህ ፕሮጀክቶች ሥራዎች የተጠናቀቁ አለመሆኑ፣
9. የመስኖ ግድብ ግንባታ ዕቃዎች የዋጋ ማስተካከያ በጊዜ ወይም በገንዘብ ወይም በዋጋ ማስተካከያ ማባዣዎች ገደብ አለመኖር፣
10. በግዥ ህግ ከተቀመጠው ከ25% በላይ ለግንባታ ዕቃዎች የሚደረገው የዋጋ ማስተካከያ መኖር፣
11. በፕሮጀክት አፈጻጸም ደረጃ ሳይሆን በየሎቱ ከፋፍሎ የዋጋ ማስታከያ የሚደረግ መሆኑ፣
12. በየጊዜው የገበያ ዋጋ ጥናት ስለማይጠና የዋጋ ማስተካከያው ላይ ከፍተኛ ጭማሪ የሚያደርግ መሆኑ፣
13. አንዳንድ የመስኖ ግድብ ግንባታ ፕሮጀክቶች የጥራት ችግር ያለባቸው መሆኑ፣ (የመገጭ ማዕከላዊ ግድብ በጥራት ችግር ምክንያት 75% የደረሰው ሥራ ከፈረሰ በኋላ አፈጻጸሙ ወደ 66% የወረደ መሆኑ፣)
14. ለመስኖ ግድብ ግንባታ ሥራ ሲባል ለልማት ተነሽዎች በተለያዩ ጊዜ በቅድሚ የካሳ ክፍያ ከተከፈለው ውስጥ ለተጠቃሚዎች የደረሳቸው መሆን አለመሆኑ ማረጋገጫ ያልቀረበባቸው 210,861,440.22 ብር ያልተወራረደ መሆኑ እና ከ2015 ዓ.ም ጀምሮ በ6 ፕሮጀክቶች 1,594 ሰዎች ብር 824,325,909.38 ካሳ እንዲከፈላቸው የተጠየቀ ቢሆንም እስካሁን ድርስ ያልተከፈላቸው መሆኑ፣ ለአብነት የአጅማ ጫጫ ፕሮጀክት ሥራ በ4 ዓመት ሥራ አፈጻጸም 64% የደረሰ ቢሆንም ካሳ ክፍያ ባለመከፈል ምክንያት ለመቆም የተቃረበ መሆኑ፣
15. በአፈጻጸማቸው ለበርካታ ዓመታት ለዘገዩ ፕሮጀክቶች ተጠያቂ አካል አለመኖር (በተቋራጩ ጉድለት ላይ የውል እርምጃዎችን አለመውሰድ)፣ (መገጭ ግድብ እና አርጆ ዲዴሳ ግድብ ግንባታ ፕሮጀክቶች፣)
16. ውሎችን ያለአግባብ ማሻሻል ወይም መቀየር፣ በውሉ ላይ ከነበረው ከ20% ቅድሚያ ክፍያ ወደ 30% ከፍ ማድረግ፣ የዋጋ ማስተካከያ ውሎችን መቀየር ወዘተ…፣ (from price adjustment not applicable to applicable)፣ from unlotting to lotting፣ ( ወይቦ እና ቋጦ ፕሮጀክቶች)፣
17. ፕሮጀክቶችን ያላአግባብ ማቋረጥ እና ቶሎ ወደ ሥራ እንዲገቡ አለማድረግ፣ (አርጆ ዲዴሳ፣ካሊድ ዲጆና ወወቦ)
18. ለመስኖ ግድብ ፕሮጀክት ሥራዎች በቂ ያልሆነ ክትትል እና ቁጥጥር ስርዓት መኖር፣
19. እስከ ሰኔ 2016 ዓ.ም ድረስ በጠቅላላው ብር 15,388,404,013.86 ተሰብሳቢ ሂሳብ እና ብር 2,472,542,685.09 የተከፋይ ሂሳብ በወቅቱ ያልተሰበሰበ እና ያልተከፈለ የፕሮጀክት ሂሳብ መኖር፣
20. በሚ/ር መ/ቤቱ የተጠናቀቁ የመስኖ ልማት ፕሮጀክቶች ወደ ሥራ የገቡት እና ያለሙት መሬት በአማካይ 17.4% መሆን የመስኖ ፕሮጀክቶች ውጤታማነት ዝቅተኛ መሆኑ ዋና ዋና ግኝቶች ናቸው፡፡

## ምዕራፍ አምስት

## የቀረቡ ምክረ ሐሳቦች

ከላይ የሚታዩ ለሙስናና ብልሹ አሰራር ተጋላጭ የሆኑ ችግሮችንና የችግሩ መንስዔዎችን ለመቀነስ የሚያስችሉ ምክረ ሀሳቦች በመጠቀም የዘርፉን የመስኖ ልማት አፈጻጸም የሚሻሻልበትን መንገድ እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

- በግዥ አፈጻጸም ገንዘብ ሊያስገኝ የሚችለውን ጥቅም ለማስገኘት ወይም ቁጠባን፣ የአፈጻጸም ብቃትንና ውጤታማነትን ለማረጋገጥ፣ ፍትሐዊነትን (ከአድሎ ነፃ) የሆነ አፈጻጸም ለማስፈን የሚያስችለውን ግልጽ የግዥ ዘዴን ጥቅም ላይ ማዋል፡፡
- የዲዛይን እና የሱፐርቪዥን ሥራ የሚሰሩ አማካሪዎች በተቻለ መጠን ሚዛኑን የጠበቀ የቁጥጥር ሥራ (Check and balance) ለመስራት የሚያመች እንዲሆን፣ ግልጽነትና ተጠያቂነትን ለማስፈን እና የጥቅም ግጭትን ለመከላከል እንዲቻል ሁለቱም የማማከር ሥራዎች በተለያዩ አማካሪዎች የሚሰራበት ሁኔታ ቢኖር፣
- የመስኖ ግድብ ግንባታ ፕሮጀክት በወቅቱ (በታቀደለት ጊዜ) እና በተያዘለት በጀት እንዲጠናቀቅ ለማድረግ እና የተቋራጮችን የሥራ ክብደትን፣ የጊዜ መጣበብን፣ የማሽነሪዎች እና የሰው ሃይል እጥረት ለመቅረፍ በተመሳሳይ ጊዜ የሚይዙትን የፕሮጀክት መጠን መወሰን እና ገደብ መስጠት፣
- የተቋራጮች ግዥ ሲፈፀም የምህንድስና ግምት ሳይሰራ በድርድር ከመፈፀም ይልቅ በመረጃ፣ በዝርዝር ጥናት እና ዲዛይን ላይ የተመሰረተ ትክክለኛ የጊዜ እና ዋጋ ግምት መስጠት፣
- በግንባታ ላይ የሚገኙ ፕሮጀክቶች የግዥ ሰነዶች የፋይናንስ ህግ በሚፈቅደው መሰረት ለተወሰነ ጊዜ በአግባቡ ተደራጅተውና ተጠብቀው የሚቆዩበትን አሰራር መዘርጋት፣
- የፕሮጀክት አዋጭነት እና የዲዛይን ዝርዝር ጥናት በአግባቡ እና በጥራት በማዘጋጀት፣ ግዥዎችን በግልፅ ጨረታ በመፈፀም፣ የካሳ ክፍያዎችን በወቅቱ በመፈፀም፣ የፋይናንስ እጥረት ችግሮችን በመቅረፍ፣ የፕሮጀክት ሥራ ከመጀመሩ በፊት ኮንትራክተሩ የተቀናጀ የፕሮጀክት ዕቅድ በማቀድ እና መርሃ ግብር በማዘጋጀት አስቀድሞ በባለድርሻ አካል የሚፀድቅበትን ስርዓት በመዘርጋት ፕሮጀክቶችን በተቀመጠላቸው የማጠናቀቂያ ጊዜ፣ በጀት እና ጥራት ማጠናቀቅ፣

- መንግስት ከፍተኛ ተጨማሪ ጊዜ እና ወጪ እንዳያወጣ ፕሮጀክቶችን ለተቋራጮች በሎት ከፋፍሎ (spilit) አለመስጠት፣ በጥቅል ግዥ የተሰጠን ፕሮጀክት ሥራ ያላአግባብ በሎት ከፋፍሎ በግዥ ከመስጠት መቆጠብ፣
- የዋጋ ማስተካከያዎች በጊዜ ወይም በገንዘብ ወይም በዋጋ ማስተካከያ ማባዣዎች ገደብ የሚደረግበት አሰራር መዘርጋት፣
- በመንግስት የግዥ ህግ 25 በመቶ በተቀመጠው የዋጋ ማስተካከያ ገደብ መሰረት ተግባራዊ ማረግ፣
- ለግንባታ ዕቃዎች የሚደረገው የዋጋ ማስተካከያ በየሎት ከፋፍሎ ማስተካከል ሳይሆን በፕሮጀክት አፈፃፀም ደረጃ የሚተገበርበትን አሰራር መዘርጋት፣
- ለዋጋ ማስተካከያ እንደማስረጃ የሚጠቀሙበት የገበያ ዋጋ ጥናት ባለሙያ በመመደብ እና በየጊዜው ጥናት በማድረግ የሚመጣውን የዋጋ ማስተካከያ ከፍተኛ ወጪ የሚቀንስበትን አሰራር መዘርጋት፣
- የፕሮጀክቶች መዘግየት ዋና ምክንያት የሆነውን የካሳ ክፍያን በወቅቱ መክፈል፣ እንዲሁም ቅድሚያ ተከፍለው ያልተወራረዱ የካሳ ክፍያዎች እንዲወራረዱ በማድረግ ግልጽነትና ተጠያቂነትን ማረጋገጥ፣
- በተቀመጠው ውል መሰረት ለፕሮጀክቶች አፈጻጸም መዘግየት ተጠያቂ አካል እንዲኖር ማድረግ እና ጉድለት በሚፈጥር አካል ላይ በተቀመጠው ውል መሰረት እርምጃዎችን መውሰድ፣
- ከተቀመጡ የፕሮጀክት የውል ስምምነቶች ውጪ ያላግባብ የሚደረጉ የውል ማሻሻያዎች ክትትልና ቁጥጥር የሚደረግበት አሰራር መዘርጋት፣
- የመስኖ ግድብ ግንባታ ፕሮጀክቶች በተያዘላቸው ጊዜ እና በጀት እንዲጠናቀቁ የሚያስችል በስትራቴጂ የተደገፈ የክትትል እና የቁጥጥር አሰራር መዘርጋት፣
- የመንግሥት ገንዘብ ለብክነትና ለጥፋት እንዳይዳረግ የተሰብሳቢ እና የተከፋይ ሂሳቦች በወቅቱ እንዲሰበሰብ እና እንዲከፈል ማድረግ የሚቻልበት አሰራር መዘርጋት፣
- የፕሮጀክቶችን ውጤታማነት ከፍ ለማድረግ የተጠናቀቁ የመስኖ ልማት ፕሮጀክቶች ወደ ሥራ የሚገቡበትን አሰራር በመዘርጋት ለሀገር ኢኮኖሚ ግንባታ የበኩላቸውን አስተዋጽኦ እንዲያበረክቱ በማድረግ ሙስናና ብልሹ አሰራርን ሊከላከሉ የሚችሉ ምክረ ሀሳቦች ቀርበዋል፡፡

## የጥናቱ ሪፖርት ዝግጅት እና ምክክር መድረክ ዝግጅት፣

የመስኖ ልማት ፕሮጀክት የውል አስተዳድር ጥናት ሪፖርት ከተዘጋጀ በኋላ ከመስኖ እና ቆላማ አካባቢ ሚ/ር መ/ቤት ከሚመለከታቸው የበላይ ሀኃላፊዎች እና ባለድርሻ አካላት ጋር ውይይትና ምክክር ይደረጋል፡፡

ከውይይት በኋላ በሚገኘው ግብዓት መሰረት የተስተካከለ ሪፖርት በማዘጋጀት የጥናቱ ግኝቶች ተግባራዊ የሚደረጉበትን ስትራቴጂ እንዲያዘጋጁ እና ምክረ ሀሳቦች ተግባራዊ እንዲደረጉ ድጋፍና ክትትል ይደረጋል፡፡

## ማጠቃለያ

የመስኖ ግድብ ግንባታ ፕረጀክቶች በተለያዩ ምክንያቶች በተመደበላቸው የጊዜና የበጀት ግመት መሰረት ባለመጠናቀቃቸው መንግስት አላስፈላጊ ተጨማሪ ወጪ እንዲያወጣ አድርጎታል፡፡

ለፕሮጀክቶች መዘግየት ምክንያት የተለያዩ አካላት ድርሻ ቢኖርም ከፍተኛውን ድርሻ 42% የሚይዘው የፕሮጀክቱ ባለቤት ነው፡፡ ለፕሮጀክቱ መዘግየት ዋና ዋና ምክንያቶች፡- የአዋጪነት ጥናት፣ ዝርዝር ጥናት እና ዲዛይን በአግባቡ አለማዘጋጀት፣ ባልተጠናቀቀ ዲዛይን ውል መዋዋልና ግንባታ ማካሄድ፣ በተደጋጋሚ የዲዛይን ለውጥ ማድረግ፣ የመስኖ ልማት ፕሮጀክቶችን ወሰን ደጋግሞ መቀየር፣ አንድ ድርጅት በተመሳሳይ ጊዜ በርካታ ፕሮጀክቶችን እንዲሰራ ማድረግ፣ የሥራ ትዕዛዝን መቀየር፣ የካሳ ክፍያ በወቅቱ አለመክፈል፣ የፋይናንስ ክፍያ ማዘግየት ወይም በወቅቱ አለመክፈል፣ የፕሮጀክት አፈጻጸም ክትትልና ቁጥጥር ማነስ የፕሮጀክት ግንባታዎች እንዲዘገዩ ከሚያደርጉ ምክንያቶች የተወሰኑት ናቸው፡፡ ይህም የመስኖ ግድብ ግንባታ ፕሮጀክት ውል አስተዳደር ግልጽነት የጎደለው መሆኑን ያሳያል፡፡

ከላይ የተዘረዘሩትን የችግር ምክንያቶችን ለመፍታት ከቀረቡ ምክረ ሀሳቦች ውስጥ የግታባታ ግዥ በግልጽ ጨረታ ዘዴ መፈፀም፣ ለፕሮጀክቶች ተገቢና ትክክለኛ የጊዜና የወጪ ግምት ማስቀመጥ፣ ፕሮጀክቶች በተቀመጠላቸው ጊዜ፣ በጀት እና ጥራት መጠናቀቅ እንዲችሉ የመስኖ ልማት የፕሮጀክት ዕቅዶች ስትራቴጂ እቅድና መርሃ ግብር በማዘጋጀትና በባለድርሻ አካላት እንዲፀድቅ በማድረግ ተገቢውን የፕሮጀክት አፈጻጸም ክትትልና ቁጥጥር ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

## ማጣቀሻ፡-

1. የመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 ዓ.ም፣

2. የፌደራል መንግስት የግዥ አፈጻጸም መመሪያ ሰኔ 2002 ዓ.ም፣
3. የመስኖና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር መዋቅራዊ አደረጃጀት እና የሰው ኃይል ፍላጎት ህዳር/2014 ዓ.ም፣
4. የመስኖና ቆላማ አካባቢ ሚ/ር የ10 ዓመት መሪ ዕቅድ( ከ2013—2022) ፣
5. የመስኖና ቆላማ አካባቢ ሚ/ር የመካከለኛ ዘመን (ከ2016-2018) የልማትና የኢንቨስትሜንት ዕቅድ መጋቢት 2015 ዓ.ም፣
6. የካሳ ክፍያ አዋጅ (የመሬት ይዞታ የሚለቀቅበት፣ ካሳ የሚከፈልበት እና ተነሺዎች መልሰው የሚቋቋሙበትን ሁኔታ ለመወሰን የወጣ (ማሻሻያ) አዋጅ ቁጥር 1336/2024 ዓ.ም
7. የፌዴራል ዋና ኦዲተር የፌዴራል መንግሥት መ/ቤቶች የ2014 በጀት ዓመት የፋይናንስና ሕጋዊነት ኦዲት እና የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት ሰኔ/ 2015 ዓ.ም፣
8. የመስኖና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር የ2017 በጀት ዓመት የተከለሰ ዕቅድ ጥቅምት 2017 ዓ.ም፣
9. የመስኖና ቆላማአካባቢ ሚኒስቴር የ2017 በጀት ዓመት የ1ኛ ሩብ ዓመት የዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት ጥቅምት/2017 ዓ.ም፣
10. በፌደራል የሥነ ምግባር እና የፀረ ሙስና ኮሚሽን የመስኖ እና ቆላማ አካባቢ ዘርፍ የሙስና ስጋት ጥናት 2015 ዓ.ም
11. በውሃና ኢነርጂ ሚ/ር እና በኦሮሚያ ውሃ ሥራዎች ድርጅት መካከል የተደረገ የአርጆ ዲዴሳ የመስኖ ግድብ እና ተያያዥ ልማት ፕሮጀክት የውል ስምምነት ሰነድ ጥር 23/2003 ዓ.ም፣
12. በውሃ ሃብት ሚ/ር እና በውሃ ስራዎች ኮንስትራክሽን ድርጅት መገጭ ግዴብ ግንባታ ፕሮጀክት መስከረም /2001 ዓ.ም የተደረገ የውል ስምንነት፣
13. የምክር አገልግሎት እና የግንባታ ስራዎች ግዥ አፈጻጸም ሰነዶች፣
14. የውል ስምምነት ሰነዶች፣ የውል ማሻሻያዎች፣ የዋጋ ማሻሻያዎች፣ የፋይናንስና የካሳ ክፍያ ሰነዶች፣
15. የመገጭ ፕሮጀክት የተቋረጠበት ሪፖርት፣ ሚያዝያ 2016 ዓ.ም.
16. ካሊድ ዲጀ የመጀመሪያው የውል ስምምነት ግንቦት 27/2012 ዓ.ም
17. የካሊድ ዲጀ የአናት ስራ እና የመስኖ መሠረተ ልማት ፕሮጀክት ውል ስምምነት ግንቦት 27 /2012 ዓ.ም
18. መገጭ ግድብ ፕሮጀክት ዋናው ውል ስምምነት ነሐሴ 2000 ዓ.ም
19. የመገጭ ፕሮጀክት የውል ማራዘሚያ ማሻሻያ ቁጥር 09 መጋቢት 26 /2013 ዓ.ም
20. ካሊድ ዲጀ የአማካሪ ውል ስምምነት ሰነድ ሰኔ/2012 ዓ.ም
21. ካሊድ ዲጀ የውል ስምምነት ማሻሻያ ቁጥር 01 ጥር 9 /2015 ዓ.ም
22. ቄጦ የውል ስምምነት ግንቦት 6 /2013 ዓ.ም
23. ቄጦ የውል ማሻሻያ ቁጥር 01 ግንቦት 6 /2013 እና ቁጥር 02 ጥቅምት 2016 ዓ.ም
24. የወይቦ ፕሮጀክት ሎት 2 የውል ስምምነት ግንቦት 6 /2013 ዓ.ም
25. የወይቦ የውል ስምምነት ማሻሻያ ቁጥር 01 መስከረም 29/ 2016 ዓ.ም
26. የፕሮጀክቶች የአፈጻጸም ደረጃ ሪፖርት ሰነዶች ተዳሰዋል፡፡